# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 165 የካቲት 15 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## በሶማሌ ክልል ሦስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ ባለሀብቶች ፈቃድ ተሰጠ

**ጌትነት ምሕረቴ**

ጅግጅጋ፡- በሶማሌ ክልል ባለፉት ስድስት ወራት ከሦስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ላስመዘገቡ 171 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ መሰጠቱን የክልሉ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ቢሮ አስታወቀ፡፡

በቢሮው የኢንቨስትመንት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሰይነብ ሀጂ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ ባለፉት ስድስት ወራት በዘመናዊ ግብርና፣ ኢንዱስትሪ፣ ንግድና ቱሪዝም ዘርፎች ኢንቨስት ለማድረግ ጥያቄ ላቀረቡ 171 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ እነዚህ ባለሀብቶችም ሦስት ነጥብ

በሶማሌ ክልል ሦስት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

ወይዘሮ ሰይነብ ሀጂ

## ድርጅቱ ከሆስፒታሉ ውጪ ለሚገኙ ሴቶች የድጋፍ አቅርቦቱን እንደሚያሰፋ አስታወቀ

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የሴቶች ጤና ድጋፍ በጎ አድራጎት ድርጅት በቀጣይ ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ውጪ ለሚገኙ ሴቶች የድጋፍ አቅርቦቱን እንደሚያሰፋ አስታወቀ፡፡

በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ በማህጸንና ጽንስ ትምህርት ክፍል ሐኪሞች የተቋቋመው የሴቶች ጤና ድጋፍ በጎ አድራጎት ድርጅት ትናንት ሕጋዊ ዕውቅና ማግኘቱን አስመልክቶ መርሐ ግብር

ድርጅቱ ከሆስፒታሉ .. ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አምባሳደር መለስ አለም(ዶ/ር)

## ኢትዮጵያውያን ያለ ቪዛ ክፍያ ወደ ኬንያ መግባት እንደሚችሉ ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ጉዳይ በልዩ በማየት አዲስ በዘረጋችው የጉዞ ፈቃድ ማረጋገጫ ኢትዮጵያውያን ያለ ቪዛ ክፍያ ወደ ኬንያ መግባት እንደሚችሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በሳምንቱ የተከናወኑ አበይት የዲፕሎማሲ ክንውኖችን አስመልክቶ ሳምንታዊ መግለጫ ሰጥቷል፡፡

መግለጫውን የሰጡት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ አለም (ዶክተር) እንደገለጹት፣ መልከ ብዙ የዲፕሎማሲ ሥራ የተሠራበት ሳምንት ነው።

ኢትዮጵያውያን ያለ ቪዛ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## ኢትዮጵያ የናይል ተፋሰስ ትብብርን እውን ለማድረግ ግንባር ቀደምነቷን አጠናክራ ትቀጥላለች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ኢትዮጵያ የናይል ተፋሰስ ትብብርን እውን ለማድረግ ግንባር ቀደምነቷን አጠናክራ እንደምትቀጥል ተገለጸ፡፡

25ተኛው የናይል ቀን በቡሩንዲ ቡጁምቡራ እየተካሄደ ነው፡፡

በመርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ ውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶ/ር ኢ/ር ሀብታሙ ኢተፋ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የናይል ተፋሰስ ትብብርን እውን ለማድረግ ግንባር ቀደምነቷን አጠናክራ ትቀጥላለች፡፡

የናይል ቤዚን ኢኒሼቲቭ ለሩብ ክፍለ ዘመን የዘለቀው ጉዞው ሲገመገም፣ በ25 ዓመታት ጥሩ ውጤቶችን አምጥቷል ብሎ መናገር እንደሚቻል ያነሱት ሚኒስትሩ፤ በተለይ በተወሰኑ የተፋሰሱ አካባቢዎች የልማት ሥራዎችን ማከናወን መቻሉን ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ የናይል ተፋሰስ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



## በትግራይ ከ50 ሺህ ሔክታር በላይ መሬት በመስኖ ለምቷል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በክልሉ 50 ሺህ 200 ሔክታር መሬት በመስኖ መልማቱን የትግራይ ክልል ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ አሳወቀ፡፡ ስምንት መቶ ሔክታር መሬት ላይ ስንዴ እየለማ ነው።

በቢሮው የሆርቲካልቸር ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ በሪሁን አረጋዊ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በትግራይ ክልል መስኖን በመጠቀም 60 ሺህ 749 ሄክታር ለማልማት ታቅዶ እስካሁን ድረስ 50 ሺህ 200 ሄክታሩን ማልማት ተችሏል፡፡

ክልሉ መስኖን በመጠቀም አትክልት፣ ስንዴ፣ ጥራጥሬና ሌሎችም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሰብሎችን እያለማ ይገኛል ብለዋል።

ዳይሬክተሩ እንዳመለከቱት፤ በትግራይ ክልል ማልማት ከተቻለው መሬት ውስጥ አምስት ሺህ ሄክታር በቆሎ ማሳ የለማ ነው፡፡

በመስኖ ለማልማት ከታቀደው ሁለት ሺህ ሄክታር ስንዴ ውስጥም ስምንት መቶ ሄክታር ያህሉ መልማት

በትግራይ ከ50 ሺህ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል








## «በዓባይ ፕሮጀክት የታየው ትብብር የባሕር በር ተጠቃሚነትን በማረጋገጥም ሊደገም ይገባል»

**- ሽብሩ ማሞ**
**በታንዛንያ የኢትዮጵያ አምባሳደር**

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በዓባይ ግድብ ፕሮጀክት ላይ የታየውን የትብብር መንፈስ በተመሳሳይ መልኩ የባሕር በር ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ ረገድ ሊደገም እንደሚገባ በታንዛንያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሽብሩ ማሞ አስታወቁ።

አምባሳደር ሽብሩ ማሞ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ቢኖርም በሀገር ጉዳይ በተለይም በባሕር በር ተጠቃሚነት ላይ ልዩነት ሊኖር አይገባም።

መላው ሕዝብ የዓባይን ግድብ እንዲገነባ እያደረገ የሚገኘውን ያልተቋረጠ ድጋፍ ከማጠናከር ጎን ለጎን በተመሳሳይ የባሕር በር ተጠቃሚ ለመሆን ለተደረገው ስምምነትና ጥረቶች ድጋፉን ሊሰጥ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በግድቡ ግንባታ በመተባበር መንፈስ ለታሪክ የሚሻገር ሥራ ተሠርቷል ያሉት አምባሳደሩ፤ በተመሳሳይ በፕሮጀክቱ የታየውን አንድነት የባሕር በር ለማግኘት በሚደረገው ጥረትም ማሳየት እንደሚገባ አመላክተዋል።

የባሕር በር ውጥኑ ዕውን ከሆነ ቀጣናዊ ትስስራችን ስለሚያጠናክር ለሀገራዊ ዕድገት በጋራ መሥራት አለብን ብለዋል።

አምባሳደሩ እንዳስታወቁት፤ ሀገር አቅሟን አጎልብታ እንደትቀጥል ሁሉም አንድነቱን ማሳየትና የባሕር በር ባለቤት ለመሆን የሚደረገውን ጥረት መደገፍ ያስፈልጋል።

የወደብ ጉዳይ ለኢትዮጵያውያን ወቅታዊና አንገብጋቢ አጀንዳ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ ወደብ ለማግኘት አቅምንና ሀብትን አሟጦ መጠቀም አስፈላጊ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ፍላጎቶች መኖራቸውን አምባሳደር ሽብሩ አመላክተው፤ መንግሥትን መቃወም ሊኖር ይችላል፤ ነገር ግን ሕዝብና ሀገር ቀጣይነት ያላቸው በመሆኑ ለብሔራዊ ጥቅም በአንድነት መሥራት ይገባል ብለዋል።

በተለያየ መንገድ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም በሚያመጡ ጉዳዮች ላይ በስፋት መሥራት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

የባሕር በር ስምምነቱን በተመለከተ ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ሥራ መሥራትና ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በበቂ ሁኔታ ለማስረዳት ጠንካራ የዲፕሎማሲ ጥረት ማድረግ የግድ መሆኑን ጠቁመዋል።

አሁን ላይ የተነሳው የባሕር በር ባለቤትነት ጥያቄ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገር የቆየ እንጂ የአንድ ፓርቲ ጉዳይ አይደለም ያሉት አምባሳደሩ፤ የሌላ ሀገር ፓስፖርት ይዞ ስለ ኢትዮጵያ በድፍረት መናገርና የባሕር በር ጥያቄ ከማይቀበሉ ሀገራትና ግለሰቦች ጎን ተሰልፎ መቃወም ተገቢ አይደለም ብለዋል።

ለሀገራቸው ጤማና አመለካከት የሌላቸው ካልሆኑ በስተቀር የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ከመንግሥት ጋር ማያያዝና ማጣጣል በፍጹም ተቀባይነት የለውም ሲሉ ተናግረዋል።

የሕዝብን ችግር ካለመገንዘብ በመነጨ ስሜት ስምምነቱን የሚቃወሙ ሀገራትና ግለሰቦች መኖራቸውን ጠቁመው፤ በወደብ ጉዳይ የተነሳውን ጥያቄ መደገፍ እንዲሁም ልዩነቶችን ብሔራዊ ጥቅምን በማይጎዳ መልኩ መፍታት እንደሚገባም አመላክተዋል።


እንደ አምባሳደር ሽብሩ ገለጻ፤ በኢትዮጵያ እየተገኙ ያሉ የዲፕሎማሲ ድሎች አመርቂ ናቸው። ይበልጥ በውጭው ዓለም ተቀባይነትን ለማግኘት ሀገር ውስጥ ያለውን ግጭት መፍታት ያስፈልጋል።

ግጭቶችን በመፍታት፣ የሚፈናቀሉ ሰዎችን ቁጥር በመቀነስ፣ ልማትን በማፋጠን፣ የሀገርን ገጽታ በመገንባትና የሰብአዊ ቀውስን በመቀነስ አንድነትን ማጠናከርና የሀገርን ዕድገት ማስቀጠል እንደሚገባ አምባሳደር ሽብሩ አስረድተዋል።

# በቢሾፍቱ ከተማ ዲጂታል የአድራሻ
## ሥርዓት ተተገበረ

**ተስፋ ፈሩ**

ቢሾፍቱ፡- በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነው ዲጂታል የአድራሻ ሥርዓት ፕሮጀክት ተጠናቆ በቢሾፍቱ ከተማ ተግባራዊ መደረጉን የስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ትናንት አስታወቀ።




የዲጂታል ሥርዓቱን ያስጀመሩት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) በመርሐግብሩ ላይ እንደተናገሩት፤ የአድራሻ ሥርዓት ሳይኖር ዲጂታል ኢኮኖሚን መገንባት የማይታሰብ ነው።

ዲጂታል የአድራሻ ሥርዓት ማንኛውንም አስተዳደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ለሁሉም ተደራሽ ለማድረግ አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል ብለዋል።

በ73 ትላልቅና መካከለኛ ከተሞች ሥርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ እቅድ ተይዞ እየተሠራ እንደሚገኝ የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ የቢሾፍቱ ከተማ ዲጂታል የአድራሻ ሥርዓት በዚህ መሠረት የተከናወነ መሆኑን ገልፀዋል።

የስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ዋና ዳይሬክተር አብዲሳ ይልማ በበኩላቸው፤ ዲጂታል የአድራሻ ሥርዓቱ ኢትዮጵያ እያስመዘገበች ያለውን እድገት በዘላቂነት ለማስቀጠል ኢንስቲትዩቱ ከሚተገብራቸው ለውጥ አምጪ ፕሮጀክቶች መካከል አንዱና ዋነኛው ነው ብለዋል።

የአድራሻ ሥርዓቱ ከፍተኛ በጀት፣ የከተማ መስተዳድሮችን ቁርጠኝነትና የነዋሪዎችን ትብብር የሚጠይቅ በመሆኑ ሌሎች ከተሞች ከወዲሁ ዝግጅት እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርበዋል።

የቢሾፍቱ ከተማ ከንቲባ አቶ አለማየሁ አሰፋ ዲጂታል የአድራሻ ሥርዓቱ የቱሪዝም ከተማ ለሆነችው ቢሾፍቱ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ተስፋ ሰጪ ነው። ለከተሞች እድገት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥርና እንገነባለን ለምንለው ስማርት ሲቲ መሠረት የሚጥል ነው ብለዋል።

በስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩቱ የዲጂታል የአድራሻ ሥርዓት ሥራ አስኪያጅ አድማሴ ገበየሁ፣ የቢሾፍቱ ዲጂታል የአድራሻ ሥርዓት ከ 10 ሺህ በላይ ቤቶች ማካተቱን አመላክተዋል፡፡

ሀገርኛ ቋንቋዎችን መሠረት አድርጎ የተሠራ በመሆኑ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማርኛና ኦሮምኛ ቋንቋዎች አገልግሎት እንደሚሰጥ ገልፀዋል።

ትናንት ተመርቆ ሥራ የጀመረው የዲጂታል አድራሻ ሥርዓት በከተማዋ የሚገኙ ተቋማትን እና የመኖሪያ ቤቶችን ትክክለኛ መገኛ ሥፍራ በማመላከት ነዋሪዎች ከቦታ ቦታ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ለማቅለልና ለማቀላጠፍ ጉልህ አስተዋጽዖ እንደሚያበረክት ተጠቁሟል።


በተጨማሪም የተቀላጠፈ የመሠረተ ልማት ዝርጋታና ጥገና አገልግሎት ለመስጠት፣ ፈጣን የአስቸኳይ ጊዜ ርዳታና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ለማድረስ፤ መንግሥታዊ አገልግሎቶችን ለማዘመን እንዲሁም የኤሌክትሮኒክ ግብይትን እና ማኅበራዊ አገልግሎትን ለማሳለጥ መሠረት ይሆናል ተብሏል።

የስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት በቢሾፍቱ ከተማ የጀመረውን ዲጂታል አድራሻ ሥርዓት በመላ ሀገሪቱ ተግባራዊ በማድረግ ሁሉንም ከተሞችና ገጠሮች ለመሸፈን ውጥን ይዟል።

በምርቃት ሥነሥርዓቱ ላይ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች አመራሮች፣ ከንቲባዎች፣ አባገዳዎች እና የቢሾፍቱ ከተማ ነዋሪዎች ተሳትፈዋል።

# «የዓድዋ ድል መታሰቢያ በዓድዋ የተሳተፉ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን የተካሱበት ነው»

**- ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን**
**የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት**



**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የዓድዋ ድል መታሰቢያ በዓድዋ የተሳተፉ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን የተካሱበት ነው ሲሉ የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ገለጹ።

የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ከአራቱም አቅጣጫ ተምመው በዓድዋ የተሳተፉ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን የተካሱበት ነው።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሃሳብ አመንጪነት ታቅዶ፣ ተነድፎ ተሠርቷል ያሉት ልጅ ዳንኤል፤ የበርካታ ሚዲያዎችንና ግለሰቦችን ጫና በመቋቋም አጠናቅቀው ለምረቃ አብቅተዋል ብለዋል።

የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመለያየትና ለማፋጀት በሀገሪቱ የልማት ሥራ እንዳይሠራ፣ ሰላም እንዳይኖር ሲደረግ መቆየቱን ጠቅሰው፤ አዲሱ ትውልድ የዓድዋ ድል መታሰቢያን ገንብቶ ለሕዝብ ማቅረቡ ከኢትዮጵያ አልፎ ለአፍሪካና ዓለም የሚተርፍ መሆኑን ገልጸዋል።

የድል መታሰቢያው መገንባት አጼ ምኒልክን ጨምሮ አርበኞቻቸው፣ ጀኔራሎቻቸውና በጦርነቱ የተሳተፉ ኢትዮጵያውያን የተካሱበት ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ይህን ያዩ በአንድ በኩል ደስ ይላቸዋል በሌላ በኩል ደግሞ ጠላቶቻችን ያንገፈግፋቸዋል ብለዋል።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ የተሠራበት ቦታ ቀደም ሲል ላልተገባ ዓላማ ሲውል መቆየቱን ጠቅሰው፣ መዲናዋን የማይመጥን ተግባር ሲሠራበት የቆየ አካባቢ መሆኑን ገልጸዋል።

ባለፉት ዓመታት የዓድዋን በዓል ለማክበር ብዙ ችግሮች እንደነበሩ ጠቅሰው፤ በአለፈው ዓመት የሀገር መከላከያ ሠራዊት የዓድዋን መታሰቢያ በዓል ማክበሩን አስታውሰዋል።

መንግሥታት በተለዋወጡ ቁጥር የተለያዩ ታሪኮች ሲነገሩ ስም በማጥፋት ሕዝቡንና መሪውን ለያይተዋል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ይህም ለጠላቶቻችን የተመቸና በር የከፈተ ነበር ብለዋል።

የቀደምት አባቶችን ታሪክ ለወጣቶች በማስተማር ወደ ፊት መሄድ ሲቻል ሀገር ሰላም እንደሚሆን ገልጸው፤ በአሁኑ ጊዜ መሆን የሚገባውን ነገር ለኢትዮጵያ ጥሩ በሚያስብ ሰው ከላይ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

መንግሥት የቀድሞውን ታሪክ እያስከበረና እያሳመረ ለትውልዱ እየሰጠ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይም መንግሥት የጀመረውን ባህልን እና ታሪክን የማስጠበቅና የማስከበር ተግባሩን አጠናክሮ ሊቀጥልበት ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ዜና



አቶ ዳዊት ገበየሁ

# የዳውሮ ዞን

## ሕዝብ የመልማት ጥያቄዎች ምላሽ እያገኙ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

ታርጫ፡- ከለውጡ ወዲህ የዳውሮ ዞን ሕዝብ የመልማት ጥያቄዎች ምላሽ እያገኙ መሆኑን የዞኑ አስተዳደር አስታወቀ።

የዳውሮ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ዳዊት ገበየሁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዳውሮ ዞን በሕዝብ ጥያቄ መሠረት በቅርቡ ከተዋቀሩ አደረጃጀቶች አንዱ ነው።

በዞኑ ከለውጡ በኋላ በርካታ የኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ያሉት አቶ ዳዊት፤ በዚህም በተለያዩ ዘርፎች ውጤቶች እየተመዘገቡ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

እስከ ቅርብ ዓመታት ዳውሮ ዞን አስፋልት መንገድ የሌለበት ዞን ነበር ያሉት ኃላፊው፤ አሁን የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታዎች በተለያዩ አካባቢዎች እየተካሄዱ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ዞኑ የመደራጀት ጥያቄው ከመከበሩም በላይ የክልሉ የማኅበራዊ ክላስተር መቀመጫ እና ክልሉ የትምህርት፣ የጤና እና የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች የሚገኙበት መሆኑንም አያይዘው አንስተዋል።

የዞኑ የመልማት እና የፍትሐዊነት ጥያቄዎች እየተመለሱ መሆኑን ጠቅሰው፤ በርካታ ኢንቨስተሮች ወደ ዞኑ እየመጡ እያለሙ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

በዞኑ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች እየተሠሩ መሆኑን አያይዘው ያነሱት ኃላፊው፤ የዞኑ የመልማት ተስፋ እየሰፋ መምጣቱን አብራርተዋል።

አካባቢው በበርካታ የቱሪስት መስህቦች የተሞላ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ዳዊት፤ እነዚህን መስህቦች ወደ ዕድል መቀየር የተቻለው ከለውጡ በኋላ መሆኑን አስረድተዋል።

በዞኑ ሎማ ወረዳ የሚገኘውን ሃላላ ኬላን ለአብነት በመጥቀስም፤ የገበታ ለሀገር አንዱ አካል የሆነው ሃላላ ኬላ ፕሮጀክት የአካባቢውን ፀጋ ወደ መስህብነት በመቀየር ለዞኑ፣ ለክልሉ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ ገቢዎች እንዲገኙ መደረጉን ተናግረዋል።

የንጉሥ ሃላላ ኬላ በእጃችን እያለ ያልተመለከትነው ፀጋ ነበር ያሉት ኃላፊው፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አካባቢውን መጥተው በመጎብኘት የቱሪስት መዳረሻነቱን የሚያሰፋ ሥራ መሥራታቸውን ተናግረዋል። በዚህም ዞኑ፣ ክልሉ እንዲሁም እንዳጠቃላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ጥቅም የሚያስገኝ ሥራ ተሠርቷል ብለዋል።

የሃላላ ኬላ ፕሮጀክት ለአካባቢው የቱሪስት መስህብነትን ከመጨመር ባሻገር የአስፋልት መንገድ መሠራቱንም አያይዘው አንስተዋል።

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በዳውሮኛ ለመስጠትም ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውን አብራርተዋል።

# ትርኢቱ

## የንግድ ዘርፉን በማዘመን የሀገር ኢኮኖሚን ለማነቃቃት ይረዳል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- አዲስ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢት የንግድ ዘርፉን በማዘመን የሀገር ኢኮኖሚን ለማነቃቃት ይረዳል ሲል አዲስ አበባ ንግድ ቢሮ አስታወቀ።

26ኛው አዲስ-ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢት በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽንና ገበያ ልማት ማዕከል በትናንትናው ዕለት ተከፍቷል።

በወቅቱ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ተወካይ አቶ መከታ አዳፍሬ እንደገለጹት፤ የንግድ ትርኢቱ የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም የውጭ ኩባንያዎች የሚያመርቷቸውን ምርቶች ከሸማቹ ጋር በማስተዋወቅ የንግዱን ዘርፍ ለማነቃቃት የሚካሄድ ነው።

አዲስ-ቻምበር የንግዱን ዘርፍ በማዘመን በተለይ አሁን ሀገራችን ላይ ያለውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት እና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማነቃቃት ይረዳል ብለዋል።

ሸማቹ የሚፈልገውን ምርት በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያገኝበትን ሁኔታ ከመፍጠር ባሻገር የገበያ ትስስሩን በማጠናከር አምራቹን ከፍ ወዳለ ዕድገት የሚያመጣ ነው ሲሉ ገልጸው፤ አዲስ ቻምበር ለረጅም ዓመት አምራቾችን ለማበረታታት ሲካሄድ የቆየ ትርኢት በመሆኑ የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ከምክር ቤቱ ጋር በመቀናጀት ብዙ ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል ሲሉ አክለዋል።

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት መሰንበት ሸንቁጤ በበኩላቸው፤ አዲስ ቻምበር በተለያዩ ጊዜያት ከተለያዩ አካላት ጋር የሚያካሂዳቸው የንግድ ትርኢቶች ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የገበያ ትስስር የሚፈጥሩ ናቸው ብለዋል።



መሰንበት ሸንቁጤ

በዚህ የንግድ ትርኢት በማኑፋክቸሪንግ፣ በኢንዱስትሪው እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች ላይ የተሰማሩ አምራቾች የሚሳተፉበት ነው ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ በ26ኛው አዲስ-ቻምበር የንግድ ትርኢትም 60 የሀገር ውስጥ የንግድ ማኅበራትና ስድስት ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ተሳትፈዋል ብለዋል።

ቻምበሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ ሲካሄዱ ዋና ዓላማቸው የሚሆነው አምራች እና ሸማቾችን በማገናኘት የገበያ ትስስር መፍጠር ነው ሲሉም ገልጸዋል።

የዘንድሮ አዲስ-ቻምበር ዓለም አቀፍ ንግድ ትርኢት ተሳታፊዎች ቁጥር ቀንሷል ያሉት ዳይሬክተሯ፤ ይህ ሊሆን የቻለውም አምራቾችና ነጋዴዎች ምርቶቻቸውን ለማቅረብ ምቹ ሁኔታን ስለሚፈልጉ ነው ብለዋል።

በቀጣይ ዓመት ሀገራችን ላይ ያሉትን ችግሮች በመቅረፍ ቻምበሩ ወደ ቀድሞ ሁኔታው እንዲመለስ ይሠራል ሲሉ ተናግረዋል።

# ደም መለገስ ከሚገባቸው ሰዎች ውስጥ 0 ነጥብ 4 በመቶዎቹ ብቻ እየለገሱ ነው

**ሶሎሞን በየነ**

አዳማ፡- የዓለም ጤና ድርጅት ካስቀመጠው መስፈርት አኳያ በሀገር አቀፍ ደረጃ በበጎ ፈቃደኝነት ደም መለገስ ከሚገባቸው ሰዎች ውስጥ የሚለግሱት 0 ነጥብ 4 በመቶዎቹ ብቻ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ደምና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ደምና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ከፌዴራል የሕዝብ ግንኙነት እና ኮሙዩኒኬሽን አመራሮች እንዲሁም ከሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ አካቶ ትግበራ አመራሮች ጋር በደምና ሕብረ ህዋስ ልገሳ ዙሪያ ትናንት ውይይት አካሂዷል።

በመድረኩ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የኢትዮጵያ ደምና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አሸናፊ ታዘበው እንደገለጹት፤ ሰፊ የግንዛቤ ፈጠራና ጠንካራ ሥራ በመሠራቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከዓመት ወደ ዓመት በጎ ፈቃደኞች የሚለግሱት ደም እያደገ መጥቷል። ነገር ግን የደም ሕክምና ከሚፈልጉ ሕመምተኞች አንጻር ፍላጎቱን ለማሟላት ገና ብዙ የቤት ሥራ ይቀራል።

በተለይ ደግሞ የዓለም ጤና ድርጅት ካስቀመጠው መስፈርት አኳያ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከበጎ ፈቃደኞች መሰብሰብ ያለበት ደም እየተሰበሰበ እንዳልሆነ ዶክተር አሸናፊ አመላክተው፤ በድርጅቱ መመዘኛ መስፈርት መሠረት ከአንድ ሀገር ሕዝብ ቁጥር ውስጥ ከአንድ እስከ ሦስት በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ወይም ሰው ደም



ዶክተር አሸናፊ ታዘበው

ለጋሽ መሆን አለበት።

ከዚህ አንጻር እንደኢትዮጵያ ሲታይ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ በበጎ ፈቃደኝነት ደም መለገስ ካለባቸው ሰዎች ውስጥ የሚለግሱት 0 ነጥብ 4 በመቶዎቹ ብቻ ናቸው ብለዋል።

ዶክተር አሸናፊ፤ በአንድ ሀገር ደህንነቱ የተጠበቀ ደምና የደም ተዋጽዖ መኖር በደም እጥረት ምክንያት የሚከሰተውን የጤና መታወክና የሕይወት መጥፋትን በእጅጉ እንደሚታደግ ጠቅሰው፤ «ደህንነቱ የተጠበቀ ደም እና የደም ተዋጽዖ አቅርቦት ተረጋገጠ» ማለት የሚቻለው የሚፈለገው የደም መጠን ሙሉ በሙሉ ከበጎ ፈቃደኛ ደም ለጋሾች ሲሰበሰብና በማንኛውም ሁኔታ፣ በየትኛውም ጊዜና ቦታ በዓይነት፣ በብዛትና በጥራት የሚፈለገውን ደምና የደም ተዋጽዖ ማቅረብ ሲቻል እንደሆነ ያስረዳሉ።

ባለፉት ስድስት ወራት በተሠራው ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫና ጠንካራ ሥራም እንደ ሀገር በግማሽ በጀት ዓመት ከበጎ ፈቃደኛ ደም ለጋሾች 202 ሺህ 509 ዩኒት ደም ለመሰብሰብ ታቅዶ 169 ሺህ 288 ዩኒት ደም መሰብሰቡን ዶክተር አሸናፊ ጠቁመዋል።

ከተሰበሰበው ደም ውስጥ 43 ሺህ 277 ዩኒት ደም የተሰበሰበው ከአዲስ አበባ መሆኑን አብራርተዋል።

ዶክተር አሸናፊ አያይዘው እንደገለጹት፤ በስድስት ወራት ውስጥ 200 የሚሆኑ በጎ ፈቃደኞች ከህልፈት ሕይወታቸው በኋላ የዓይን ብሌናቸውን ለመለገስ ቃል ገብተዋል።

በተጨማሪም 114 የዓይን ብሌን በመሰብሰብ ሁሉንም በየሆስፒታሉ የዓይን ብሌን ልግሳ ሲጠባበቁ ለነበሩ ታካሚዎች መሠራጨቱን ገልጸዋል።

መጪዎቹ ወራቶች የሕዝበ ክርስቲያኑና የመስሊሙ ማኅበረሰብ የጾም ወቅት በመሆኑ የደም እጥረት እንዳይከሰት ማኅበረሰቡ የተለመደውን ሕይወት የማስቀጠልና ብርሃን የመመለስ ሰናይ ተግባሩና አጠናክሮ እንዲያስቀጥል አሳስበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በወንድማማችነት እና በአፍሪካዊ መንፈስ የተቃኘ ተምሳሌታዊ ጉርብትና!

በኢትዮጵያና በኬንያ መካከል ያለው ከጉርብትና ያለፈ ግንኙነት ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረ ነው። በብዙ መልኩ የሁለቱን ሀገራት ሕዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት ያረጋገጠ፣ በሀገራቱ ሕዝቦች መካከል ያለውን ወንድማማችነት በማጠናከር የቤተሰባዊነት መንፈስ መፍጠር ያስቻለ ነው።

ከጅምሩ በወንድማማችነትና በአፍሪካዊ መንፈስ የተቃኘው የሁለቱ ሀገራት ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ግንኙነት በየዘመኑ እያደገና ዘመኑን በሚመጥን እሳቤ እየዳበረ የሀገራቱን ሕዝቦች ወንድማማችነት እና የጋራ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ዓመታትን አስቆጥሯል።

ይህ የሀገራቱ ሕዝቦች ድንበር ከመጋራት ባለፈ፤ በባህል፣ በቋንቋ እና በታሪክ የተሳሰረ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ግንኙነታቸው እና፤ ግንኙነታቸው የፈጠረው መተማመንና ወዳጅነትም በቀጣናው እንደ ማሳያ ሊጠቀስ የሚችል እንደሆነም ብዙዎች የሚስማሙበት እውነታ ነው።

በተለይም ከኬንያ ነፃነት ማግስት ጀምሮ በሀገራቱ መካከል የነበረው ግንኙነት፣ አፍሪካዊ ወንድማማችነትን መሠረት ያደረገ፤ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ በሀገራቱ ሕዝቦች መካከል የነበረውን የቆየ ግንኙነት በአዲስ መልክ፤ አፍሪካዊ በሆነ እሳቤና መንፈስ መቃኘት ያስቻለ ነው።

ሀገራቱ በአንድ በኩል በቅኝ አገዛዝ ውስጥ የነበሩ አፍሪካውያን ወንድማማችነትንና የነፃነት ትግል በመደገፍ፤ በሌላ በኩል ትግሉ ተቋማዊ አቅም እንዲያገኝ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እውን እንዲሆን ያደረጉት የተቀናጀ ትግልም፤ በአፍሪካውያን የነፃነት ትግል ውስጥ ትልቅ ስፍራ እንዲያገኙ ያደረጋቸው ነው።

ይህ እውነታ በወቅቱ የነበሩትን የሀገራቱን መሪዎች የአፍሪካ አባት የሚል ከፍ ያለ ስም ያጎናጸፋቸው፤ የሀገራቱ ጉርብትና ከድንበር መጋራት ባለፈ፤ በነፃነትና በወንድማማችነት መንፈስ የተገራ እና ለዚሁ እውነታ የተገዛ ስለመሆኑም እስከዛሬ የመጡበት መንገድ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ሰሞኑን በአዲስ አበባ የተካሄደው 36ኛው የኢትዮጵያና ኬንያ የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ እና በስብሰባው ማጠቃለያ ላይ የተደረሰበት ስምምነትም ይህንን ዘመን ተሻጋሪ የሀገራቱን ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ በማሳደግ፤ የሀገራቱን ሕዝቦች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት የሚያሳድግ እንደሚሆን ይታመናል።

ስምምነቱ በሀገራቱ መካከል የቆየውን ጠንካራ የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በሁሉም መልኩ በላቀ ደረጃ ማስቀጠል የሚያስችል፤ በውጭ ጉዳይና መከላከያ ዘርፎች፣ በንግድና ኢንቨስትመንት፤ በማኅበራት ዘርፎች ለጋራ ተጠቃሚነት አብረው መሥራት የሚያስችላቸውን ዕድል የሚፈጥር ነው።

ሀገራቱ ከፍ ባለ ቁርጠኝነት የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ባደረገ መልኩ አብሮ ለመሥራት የጀመሩት አዲስ መነቃቃት፤ በቀጣይም የጋራ በሆኑ የአየር ንብረት ለውጥ፣ ሽብርተኝነት፣ ሥራ አጥነት፣ ሕገወጥ ስደትና መሰል ችግሮች ዙሪያ ውጤታማ ሥራዎችን ለመሥራት የተሻለ አጋጣሚ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

በተለይም አሁን ባለንበት ዓለም አቀፋዊ እውነታ፤ ሀገራት ብሔራዊ ጥቅሞቻቸውን በተሻለ መልኩ ለማስጠበቅ ከተናጠል ይልቅ በጋራ መንቀሳቀስ እንደ ዋነኛ ስትራቴጂ እየተወሰደ ባለበት ሁኔታ በሀገራቱ መካከል እየታየ ያለው አዲስ የትብብር ግንኙነት ብሔራዊ ጥቅሞቻቸውን በተሻለ መልኩ ለማስጠበቅ እንደሚረዳ ይታመናል።

ከዚህም ባለፈ፤ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ሕዝቦች ሰላምና ልማት ለማስፈን ካለባቸው መልከ ብዙ ፈተናዎች አኳያ፤ የሀገራቱ አዲስ የትብብር መነቃቃት በአካባቢው ዘላቂ ሰላም እና ልማት ለማስፈን አስፈላጊ የሆነውን የመተማመን መንፈስ ለመፍጠር ይረዳል። የቀጣናው ሀገራት ሕዝቦች በሁለንተናዊ መልኩ የጋራ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ተጨባጭ ተሞክሮ መፍጠር ያስችላል፡፡

በአጠቃላይ የሁለቱ ሀገራት ዘመናት ያስቆጠረ በወንድማማችነትና በአፍሪካዊ መንፈስ የተቃኘው ግንኙነታቸው አሁን ላይ ኢትዮጵያ ሰጥቶ በመቀበል፤ የጋራ ተጠቃሚነት መርህ በአካባቢው አዲስ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ባህል ለመገንባት እያደረገችው ላለው ጥረት ስኬትም ትልቅ አቅም እንደሚሆንም ይታመናል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የአፍሪካን ብልጽግና ለማረጋገጥ ...

ቦጋለ አበበ

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሰረት አንግቦት ከነበረው አባል ሀገራቱን ከቅኝ ገዥዎች ነፃ የማውጣት ተልዕኮ አንስቶ እስከ ወቅታዊው የአየር ንብረት ለውጥ ድርድር በርካታ ስኬቶች አስመዝግቧል፡፡

ኅብረቱ በዓለም አቀፍ መድረኮች በተለይም የዓለም ኢኮኖሚንና የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ አንድ አቋም መያዙ ከኅብረቱ ታሪክ ተጠቃሽ ስኬቶች አንዱ ነው፡፡ የአየር ንብረት ተፅዕኖውን ለመላመድና ለመቋቋም የሚረዳትን ተገቢውን ክፍያ እንድታገኝ ኅብረቱ ውጤታማ ሥራ ሠርቷል፡፡

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ደግሞ በጸጥታው ምክር ቤት ቋሚ መቀመጫ ለማግኘት እንዲሁም የአፍሪካ ድምጽ የሚጎላበት ሚዲያ እንዲኖር የተጀመሩ እንቅስቃሴዎችም በአዎንታዊ የሚጠቀሱ ናቸው።

ይሁን እንጂ ኅብረቱ ከስድስት አስርተ ዓመታት በላይ ጉዞው ሊሻገራቸው ያልቻሉ በርካታ ፈተናዎች እንዲሁም መመለስ ያልቻላቸው የጎሉ የቤት ሥራዎች እንዳሉም መካድ አይቻልም፡፡

በበርካቶች ዘንድ ኅብረቱ ተደጋግሞ ከሚወቀስባቸው ጉዳዮች አንዱ የማስፈፀም አቅሙ ያን ያህል የተጠናከረ አለመሆኑ ነው፡፡ ለዚህ አንደኛው ምክንያት ተደርጎ የሚጠቀሰው ከአባል ሀገራት የሚጠበቀውን ገንዘብ በአግባቡ መሰብሰብ አለመቻሉ ነው፡፡

መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ የኅብረቱ የ2023 በጀት 654 ነጥብ 8 ሚሊዮን ዶላር እንዲሆን በዛምቢያ በተደረገ ጉባኤ ውሳኔ ተላልፎ ነበር፡፡ ከዚህ ውስጥ ከ60 በመቶ የሚልቀው በጀት ከለጋሾች እንደሚሰበሰብ በወቅቱ ይፋ ተደርጓል፡፡ ይህም ኅብረቱ ከራሱ አቅም ይልቅ የሌሎችን እጅ ጠባቂ እንዳደረገው በርካቶች ያምናሉ፡፡

ኅብረቱን ለዚህ ከዳረጉት ዋነኛው ምክንያቶች አንዱ ደግሞ ጥቂት የማይባሉት አባል ሀገራቱ ከዓመታዊ የሀገር ውስጥ ገቢያቸው ከአንድ በመቶ ያነሰውን እንኳን ማዋጣት አለመቻላቸው ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን አፍሪካ በየዓመቱ 50 ቢሊዮን ዶላር በሙስና እንደምታጣ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ 1 በመቶ የሚሆነውን እንኳን ማዳን ቢቻል የኅብረቱን የ2 ዓመት ወጪ መሸፈን ይቻላል ብለው የሚቆጩ አፍሪካውያን ብዙ ናቸው፡፡

አህጉሪቱ ዛሬም ሙስናን መሻገር አለመቻሏ፣ የእርስ በርስ ግጭቶች በሚፈለገው ደረጃ ማስቆም አለመቻሉ፣ ድህነት አሁንም የአህጉሪቱ ቀንደኛ ጠላት መሆኑ፣ የትምህርትና ጤና አገልግሎቶች ተደራሽ አለመሆንና ጥራቱም የተጓደለ መሆን፣ በኅብረቱ የሚወሰኑ ውሳኔዎች አፈጻጸም የተለያየና የሚፈለገውን ውጤት ከማስመዝገብ አኳያ ውስንነት ያለበት መሆኑ የኅብረቱና አባል ሀገራት ጉድለት ሆነው ቀጥለዋል።

ዛሬ ላይ የአፍሪካ ኅብረት ከስኬቱም ሆነ ከልምዱ ለመማር የሚያስችለው ከግማሽ ክፍለ ዘመን የበለጠ የዕድሜ ባለፀጋ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳም የወደፊት አቅጣጫውን ሲተልም ያለፈውን ጉዞ ዞር ብሎ ማየት፤ የቆመበትን ነባራዊ ሁኔታ ጠንቅቆ መረዳትና መጪውን አቅርቦ ማሰብ ይጠበቅበታል። ለዚህ ደግሞ የማስፈጸም አቅምን ማጠናከር፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ ትኩረት መስጠት፣ ተሳትፎን ማሳደግ፣ የገቢ አቅምን ማጎልበት ወሳኝ ናቸው።

የአፍሪካ ኅብረት ከነጉድለቶቹም ቢሆን ከቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተሻለ አደረጃጀትና አሠራር እንዳለው ይታመናል፡፡ ካለንበት ዘመን አኳያም ሊኖረው ይገባል፡፡ ግን በቂ ነው ብሎ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ አይቻልም፡፡ ሁሌም ዘመኑን የዋጀ የተሻለ አሠራርና አደረጃጀት መዘርጋት እንዳለበት መካሪ አያሻም፡፡

ለምሳሌ በሀገሮች ጣልቃ ያለመግባት መርህን በማሻሻል ኅብረቱ በመፈንቅለ መንግሥት የመጡ ቡድኖችን በአባልነት አይቀበልም፣ ነገር ግን በአፍሪካ አሁንም ድረስ የእርስ በርስ ግጭት የሚታይባቸው ሀገሮች ጥቂት እንዳልሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይህንኑ ችግር ሊቀርፍ የሚችልና ነባራዊ ሁኔታውን ያገናዘበ አደረጃጀትና አሠራር ሊኖረው ግድ ይላል፡፡

የአፍሪካ ኢኮኖሚ አውትሉክ መረጃ እንደሚያስቀምጠው፤ በአፍሪካ ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 25 ዓመት ያሉ ወጣቶች ከአህጉሪቱ አጠቃላይ ሕዝብ ከ70 ከመቶ በላይ ይሸፍናሉ፡፡ ከአፍሪካ ሕዝቦች የአንበሳውን ድርሻ የሚይዙት ወጣቶች መሆናቸውን የበርካታ ጥናቶች ውጤትን ማጣቀስ ይቻላል፡፡

የዓለም ባንክ ከዓመት በፊት ይፋ ያደረገው መረጃ እንደሚያሳየው በአፍሪካ 200 ሚሊዮን የሚጠጉ ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 25 የሚጠጋ ወጣቶች አሉ። ከነዚህ መካከል 60 በመቶ የሚጠጉት ሥራ ፈላጊ መሆናቸው ኅብረቱ የሚጠብቀውን ከባድ ሥራ ያሳያል፡፡ የአፍሪካ ኅብረት በዚህ ረገድ ወጣቱን የኅብረተሰብ ክፍል ማዕከል ያደረገ እድገትን ማበረታታት ግድ የሚለው ወቅት አሁን ነው፡፡

በአህጉሪቱ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ከማረጋገጥ አኳያ ብዙ የሚቀሩ ሥራዎች እንዳሉ እሙን ነው። በተለይም ወጣቶችን ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ መሠራት ያለባቸው የቤት ሥራዎች በአግባቡ አለመሰራታቸው ለማንም የተሸሸገ አይደለም፡፡

የአፍሪካ ኅብረትም በየሀገሮቹ ለወጣቶች ምን ያህል የሥራ ዕድል እንደተፈጠረ መጠየቅን የእርስ በርስ መገማገሚያ መድረኩ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ሊያደርገው ይገባል፡፡

ኅብረቱ ሊያሳካ ያሰባቸውን ግቦች እውን ማድረግ የሚቻለው በሁሉም የነቃ ተሳትፎ መሆኑ አያጠያይቅም። በመሆኑም አባል ሀገራት ችግሮችን ከመለየት ጀምሮ እስከ ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ኅብረተሰቡን በሁለንተናዊ መርሃ ግብሮች ማሳተፍ ይገባቸዋል፡፡

ይህ ሲደረግም በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ያሉ በርካታ የፈጠራ ችሎታዎችን ማውጣትና እንደ አህጉር ችግር ፈቺ ዜጎችን መፍጠር ይቻላል የሚል እምነት በብዙዎች ዘንድ አለ፡፡

በአፍሪካ በየቦታው የሚታዩ የእርስ በርስ ግጭቶች መንስኤ በዋነኛነት የሕዝብ ፍላጎት አለመሟላት ነው። በተለይም የአናሳዎች መብት አለመከበር የግጭት መንስኤ ሲሆን ይታያል፡፡ ለዚህ ደግሞ በየአካባቢው አስተዳደር ሕዝቡን በየጊዜው ማማከር ያስፈልጋል፡፡

አፍሪካ በእርዳታና በብድር ከምታገኘው ይልቅ በታክስ ማጭበርበርና ስወራ የምታጣው ከ10 እጥፍ እንደሚልቅ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ የታክስ ሕጎች ክፍተት መኖርና በሙስና የተጨማለቁ ባለሥልጣናት እንዲሁም ብቃት ያለው የሰው ኃይል አለመኖር አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓቱን በማሻሻል የአፍሪካን ነፃነት ማረጋገጥ እንደሚቻል የዘርፉ ምሁራን ደጋግመው ያነሳሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የአፍሪካን የእርስ በርስ ንግድ ማስፋፋት፤ የታሪፍና ቀረጥ ምጣኔን ማሻሻል፤ የወጪ ገበያ የምርት ዓይነቶችን ማስፋትና ሀገራቱን በመሠረተ ልማት ማስተሳሰር የየሀገራቱን የተናጠል ጥረትና የኅብረቱን አመራሮች የጋራ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ጥራት ያለው ትምህርት ማስፋፋት፤ ለዚህ የሚሆን የትምህርት መሠረተ ልማት ግንባታና የግብአቶች አቅርቦት ማሟላትን ታሳቢ ያደረገ ስትራቴጂ ነድፎ መንቀሳቀስ፤ ለዚህ የሚሆን አህጉራዊ ቁርጠኝነት መፈጠር ከአህጉሪቱ ሀገራት ሆነ ከኅብረቱ የሚጠበቅ ነው፡፡

በአጠቃላይ የአፍሪካ ኅብረት አባል ሀገራቱን በማስተባበር ካለፉት 60 ዓመታት በላይ ያለፈበትን የውጣ ውረድ ጉዞ በማጤን የተሻለ ነገን ለመገንባትና የአፍሪካን ብልጽግና ለማረጋገጥ የአፍሪካ ሀገራት ሆነ ተቋማቸው አፍሪካ ኅብረት ከትናንቱ በበለጠ መትጋት ይኖርባቸዋል።

# ድርጅቱ ከሆስፒታሉ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

አዘጋጅቷል።

በወቅቱ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅና በሆስፒታሉ የማህፀንና ፅንስ ክፍል ኃላፊ ወንድሙ ጉዱ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ማኅበሩ በቀጣይ የበጎ አድራጎት ተግባሩን ከሆስፒታሉ ውጪ ለሚገኙ ሴቶችም ተደራሽ ለማድረግ ይሠራል፡፡

የበጎ አድራጎት ድርጅቱ የማህጸንና ጽንስ ሕክምና አገልግሎት ለማግኘት ወደሆስፒታሉ መጥተው የገንዘብ ችግር ያለባቸውን እናቶች እየረዳ መሆኑን ጠቁመው፤ በቀጣይ ከሆስፒታሉ ውጪ በተለያዩ አካባቢዎች በመንቀሳቀስ ድጋፍ እንደሚያደርግ አስረድተዋል፡፡

አገልግሎቱን በማስፋፋት በተለያዩ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ለሚገኙ ሴቶች የማህጸን በር ጫፍ ካንሰርና በሌሎች ሴቶች ተጋላጭ በሆኑባቸው በሽታዎች ላይ የሕክምና አገልግሎት እና ሥልጠና እንደሚሰጥ አብራርተዋል።

የማህጸን በር ጫፍ ካንሰርን ጨምሮ ለሌሎች ህክምናዎች አንዳንድ እናቶች ወደ ሆስፒታሉ ሲመጡ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ሕክምና ለማግኘት እንደሚቸሩ አንስተው፤ ድርጅቱ በአንድ ዓመት ከስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለ70 እናቶች 150 ሺህ ብር የሚያወጣ የሕክምና አገልግሎት ሰጥቷል ብለዋል።

በመሆኑም በጎ አድራጎት ድርጅቱ የተቋቋመው በማህፀንና ፅንስ ክፍል የሚሠሩ ሐኪሞች በጋራ በመሆን ከእራሳቸው ወርሀዊ ገቢ እየተቆረጠ አቅም ላነሳቸው




ሴቶች ድጋፍ ለመስጠት ወደ ሥራ መግባታቸውን ገልጸው፤ ማኅበሩ አድጎ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሆኖ ከመንግሥት ዕውቅና ማግኘቱን አስታውቀዋል።

አሁን ላይ ድርጅቱ የሕክምና ተማሪዎች፤ ከሆስፒታሉ ውጪም መድኃኒት ቤት ያላቸውና የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት መጥተው ስለበጎ አድራጎት ማህበሩ ሰምተው የተቀላቀሉ በጎ ፈቃደኞችን ጨምሮ ከአንድ ሺህ በላይ አባላትን መያዙን አስረድተዋል።

በቀጣይም ከሆስፒታሉ ውጪ የሚገኙ ሴቶችን ጨምሮ በጤና ዘርፉ የቅድመ መከላከል ሥልጠና፣ የሙያና የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ እንደሚሠራ ተናግረዋል።

በጎፈቃደኞች የድርጅቱ አባል በመሆን ለሴቶች ጤናማነት ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ኢትዮጵያውያን ያለ ቪዛ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

በአፍሪካ ኅብረት ስብሰባ ኢትዮጵያ ከተለያዩ ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ ግንኙነቷ እንዲጠናከር ሰፊ የዲፕሎማሲ ሥራ ሠርታለች።

ወደ ኬንያ የሚደረግ ጉዞን በተመለከተ አምባሳደር መለስ እንደገለጹት፤ ኬንያ የሌላ ሀገር ዜጎች ኤሌክትሮኒክስ የጉዞ ፍቃድ ቀድመው እንዲያገኙ በማድረግ ክፍያ በመፈጸም ብቻ ወደ ሀገሯ እንዲገቡ አዲስ አሠራር ጀምራለች።

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያውያን ያለ ቪዛ ክፍያ ወደ ኬንያ መግባት እንደሚችሉ የኬንያ መንግሥት መፍቀዱን የገለጹት ቃል አቀባዩ፤ ሁለቱ ሀገራት በ1958 ዓ.ም የተስማሙት የቪዛ ማስወገድ ስምምነትም አልተሻረም ሲሉ ገልጸዋል።

ያለ ቪዛ ክፍያ ኬንያ የሚገቡት ሰባት ሀገሮች ናቸው ያሉት አምባሳደሩ፤ ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉት የምሥራቅ አፍሪካ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ አባል ሀገራት መሆናቸውን ተናግረዋል።

ይህ ዕድል ለኢትዮጵያውያን ብቻ የተሰጠ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዓመታት በፊት ኢትዮጵያ ለኬንያውያን የዚህ ዕድል ተጠቃሚ እንድትሆን አረጋግጣ እንደነበር አንስተዋል።

የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት በጊዜ ሂደት ወደፊት እየሄደ መሆኑን አመላክተው፤ ሀገራቱ ጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ ወዳጅነት መሆኑንም ገልጸዋል።

ኬንያ ለኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገር ብቻ ሳትሆን ቤተሰብ ጭምር ናት ያሉት አምባሳደር መለስ፤ በሁለቱ ሀገራት መካከል የአፍሪካ ሀገሮች የቪዛ ጉዳይ በማይታሰብበት ዘመን በ1958 ዓ.ም ኢትዮጵያና ኬንያ ቪዛ ማስወገድ ስምምነት መፈራረማቸውን እንደ አብነት አንስተዋል።

ለብዙ ኬንያውያን አዲስ አበባ የመምጣት ጉዳይ በሀገራቸው ውስጥ እንዳለ ጉዞ ቀላል መሆኑንም ጠቅሰዋል። በተመሳሳይ ከአዲስ አበባ ኬንያ መሄድ ሀገር ውስጥ መሄድ ያህል ቀላል መሆኑን ተናግረዋል።

በተጨማሪም የመከላከያ ስምምነትና የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት በመንግሥት መለዋወጥ የሚዋዥቅ አለመሆኑን ገልጸዋል። የተጠናቀቀው 36ኛው የጋራ ኮሚሽን የሚኒስትሮች ስብሰባ ይህን ግንኙነት ከፍ የሚያደርግ ነው ብለዋል።

በተያያዘ ዜና አምባሳደር መለስ እንደገለጹት፤ የአፍሪካ ኅብረት ስብሰባ በስኬት ተጠናቋል። በስብሰባው የአፍሪካ ሀገሮች ኢትዮጵያን የዓለም የፖለቲካ መዲናነት የማጽናት ፍላጎት እንዳላቸው አረጋግጠዋል።

የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ሀገር እንደ እህት ሀገር አዲስ አበባ ያላቸውን የዲፕሎማሲ መቀመጫ የበለጠ ማስፋትና የማጠናከር ፍላጎት እንዳላቸው መግለጻቸውን በመግለጫቸው ተናግረዋል።

# ኢትዮጵያ የናይል ተፋሰስ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ምንምን እንኳን ሕጋዊ አካልነት ባያገኝም፤ በአባል ሀገራት መካከል የውውይት ፎረሞችን በመፍጠር፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን በማከናወን፤ ስለተፋሰሱ ግንዛቤ በማስጨበጥና የተፋሰሱ የእውቀት ምንጭ በመሆን እያገለገለ እንደሚገኝም አብራርተዋል።

አክለውም የናይል ጉዳዮችንና የትብብር አስፈላጊነትን ለዓለምአቀፉ ማኅበረሰብ የማስተዋወቅ ሥራ በማከናወን አበረታች ሥራዎችን ማከናወኑን ገልጸዋል።

ናይል ቤዚን ኢኒሼቲቭ 25 ዓመታት ቢያስቆጥርም እስከአሁን የሽግግር መሣሪያ ብቻ ሆኖ እያገለገለ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ቋሚ ሕጋዊና ተቋማዊ ማዕቀፍ በፍጹም ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ እንዳልሆነ ያነሱት ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ፤ ቋሚ ሕጋዊ እና ተቋማዊ ማዕቀፍ የናይል ተፋሰስ አባል ሀገራት አስተዋጽኦና ተሳትፎ ቋሚና ወጥ እንዲሆንና በአባል ሀገራት የመንግሥታት መቀያየር ምክንያት ተጽእኖ ውስጥ የማይወድቅ ጠንካራ ተቋም ለመፍጠር ያግዛል ብለዋል።

እየተከበረ የሚገኘው የብር ኢዮቤልዩ በዓል አባል ሀገራት የናይል ተፋሰስ የትብብር ማዕቀፍ ስምምነትን በማጽደቅ ወደፊት ለመራመድ ወሳኝ ሰዓት መሆኑን ገልጸው፤ ኢትዮጵያም የናይል ተፋሰስ ትብብርን እውን ለማድረግ ግንባር ቀደምነቷን አጠናክራ እንደምትቀጥል አረጋግጠዋል።

የትብብር ልማትን በተመለከተ በአባል ሀገራት መካከልና በናይል ተፋሰስ የሚገኙ ሕዝቦች ከፍተኛ የመልማት ፍላጎት ቢኖርም፤ የናይል ቤዚን ኢኒሼቲቭ የልማት አጀንዳ ሊረጋገጥ አለመቻሉን ጠቅሰዋል።

በዝግጅት ሂደት ላይ የሚገኘው የናይል ተፋሰስ የኢንቨስትመንት ፕሮግራም የናይል ተፋሰስ ሕዝቦችን ፍላጎት ለማሟላት፤ ብሎም ሕይወታቸውን ለመቀየር መልካም አጋጣሚ መሆኑን አንስተዋል።

ካለፉት የናይል ቤዚን ኢኒሼቲቭ መረዳት እንደሚቻለው፤ በናይል ተፋሰስ ተጨባጭ ሁኔታ ከውጭ በሚደረጉ የፋይናንስ ድጋፎች ላይ ብቻ በመመርኮዝ ትልልቅ የልማት ሥራዎችን ለማከናወን አዋጭ ሆኖ አይታይም ያሉት ሚኒስትሩ፤ የውስጥ አቅምን ተጠቅሞ ሀብት በማሰባሰብ የተዘጋጁ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን መተግበር ይገባል ብለዋል።

# በትግራይ ከ50 ሺህ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

እንደቻለም አስረድተዋል።

ክልሉ ለመስኖ ልማቱ 100 ሺህ ኩንታል ማዳበሪያ ለገበሬዎች ለማከፋፈል አቅዶ ከእቅዱ በላይ 110 ሺህ ኩንታል ማዳበሪያ ማከፋፈሉንም አቶ በሪሁን አስታውቀዋል።

የአርሶ አደሩን የመግዛት አቅም መዳከም ተከትሎ የፌዴራል መንግሥትና ከሌሎችም ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ድጋፍ ማድረጋቸውን ተከትሎ ክልሉ ከእቅዱ በላይ ማዳበሪያ ማከፋፈል በመቻሉ በዘንድሮው ዓመት ሻል ያለ ምርት ይጠበቃል ሲሉ አቶ በሪሁን አብራርተዋል።

በተጨማሪም ለክልሉ ሁለት ሺህ የውሃ መሳቢያ ሞተሮችን ለመግዛት አቅዶ እስካሁን ድረስም አንድ ሺህ ያህሉ ተገዝተው ለአርሶ አደሩ መከፋፈላቸውን ጠቁመዋል።

በተጠቃሚዎች ዘንድ እስከ 10 ሺህ የውሃ መሳቢያ ሞተሮችን ለመውሰድ ፍላጎት ቢኖርም በበጀት እጥረት ምክንያት እንዳልተገዛ ዳይሬክተሩ ጠቅሰዋል።

በክልሉ ከጦርነቱ በፊት 27 ሺህ ያህል የውሃ መሳቢያ ሞተሮች መኖራቸውን አስታውሰው፤ አሁን ምን ያህል እንዳሉና ጥቅም ላይ መዋል እንደሚችሉ ለማወቅ ጥናቶች በመደረግ ላይ እንዳሉም አንስተዋል።

አቶ በሪሁን በክልሉ ግብርናው ዘርፍ ላይ ያሉ ተግዳሮቶችንም አንስተዋል፤ በዚህም የውሃ መሳቢያ ችግርና የዘር አቅርቦትን የጠቀሱ ሲሆን፤ 14 ሺህ ኩንታል ምርጥ ዘር ለመጠቀም የታቀደ ቢሆንም እስካሁን ግን አምስት ሺህ ኩንታል ብቻ ጥቅም ላይ እንደዋለ ተናግረዋል።

460 ኩንታል ዘርም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ለክልሉ መሰጠቱን ገልጸዋል።

# በሶማሌ ክልል ሦስት ነጥብ ስድስት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ስድስት ቢሊዮን ካፒታል ያስመዘገቡ ናቸው።

በክልሉ ኢንቨስት ለማድረግ ፈቃድ ከወሰዱ ከ171 ባለሀብቶች መካከል አብዛኞቹ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች መሆናቸውን ገልጸው፤ 14ቱ ዲያስፖራዎች መሆናቸውን እና 755 ሚሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ባለሀብቶቹ ከሚሰማሩባቸው የኢንቨስትመንት መስኮች መካከልም አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ሆቴልና ቱሪዝም፣ ኮንስትራክሽን፣ አምራች ኢንዱስትሪዎች ተጠቃሽ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ቢሮው በፍጥነት ወደ ሥራ የሚገቡ ባለሀብቶችን ከማበረታታቱና ድጋፍ ከማድረጉ በተጓዳኝም መሬት ወስደው ወደ ግንባታ የማይገቡ ባለሀብቶችን ክትትል በማድረግ ርምጃ እንደሚወስድ ተናግረዋል።

ኢንቨስትመንቶቹ በግንባታ ወቅት ለዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥሩ ገልጸው፤ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቹ ሙሉ በሙሉ ተጠናቀው ምርትና አገልግሎት መስጠት ሲጀምሩ ደግሞ 6 ሺህ 016 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥሩ ይጠበቃል ነው ያሉት።

በክልሉ የግሉ ባለሀብት በኢኮኖሚ ያለውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ፤ ይህን ምቹ ዕድል በመጠቀም ኢንቨስት ለማድረግ አሁንም በርካታ ባለሀብቶች ፍላጎት እያሳዩ መሆኑን ተናግረዋል።

መንግሥት ኢንቨስትመንት ለማበረታታት የተለያዩ ድጋፎች እንደሚያደርግ ገልጸው፤ በመሬት አቅርቦትና በመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ላይ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል። እነዚህን ችግሮች ለመፍታትም የተቀናጀ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን በየጊዜው እየተፈቱ መሆኑን አመልክተዋል።

ሌላው ከለውጡ በፊት እናለማለን ብለው ከባንክ ተበድረው ገንዘቡን ለእርሻ ኢንቨስትመንት ባላዋሉት ግለሰቦች የተያዘው መሬት በባንኮች የፍርድ ቤት እግድ



**ወይዘሮ ሰይነብ ሀጂ**

ምክንያት እስካሁን መሬቱ ማልማት አለመቻሉን ወይዘሮ ሰይነብ አመልክተው፤ ይህን ችግር በአስቸኳይ ተፈትቶ መሬቱ ለልማት እንዲውል የሚመለከታቸው አካላት አፋጣኝ መፍትሔ እንዲሰጡት ጠይቀዋል። በተለይ የዚህ ገፈት ቀማሽ ሽንሌ ዞን መሆኑንም ጠቅሰዋል።

በክልሉ አስተማማኝ ሰላም መስፈኑ፣ ለወደብ ቅርብ መሆኑ፤ መንግሥት ለኢንቨስትመንት ድጋፍ ማደረጉና የማስተዋወቅ ሥራ መሠራቱ ኢንቨስትመንት ፍሰቱ መጨመሩን ገልጸዋል።

ኢንቨስተሩ መሬቱን ከተረከበ በኋላ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ወደ ሥራ መግባት እንደሚኖርበት ጠቁመው፤ መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል ብለዋል። ባለሀብቶች ራሳቸውና ሀገራቸውን ተጠቃሚ ለማድረግ ወደ ክልሉ በመምጣት ኢንቨስት እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርበዋል።

# የ«ባሊ» ርክክብ- በጉጂ ኦሮሞ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር


ዲሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር በገዳ ሥርዓት፣

ኢትዮጵያ የባህል፣ የታሪክ፣ የተፈጥሮና የቅርስ ሀብቶች በስፋት ከሚገኝባቸው ቀዳሚ ሀገራት ተርታ ትመደባለች። ይሁን እንጂ እነዚህን ሀብቶች በሚፈለገው መጠን የማስተዋወቅ፣ የማልማትና ከሀብቱ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ አቅም አሁንም ድረስ እንዳልጎለበተ ይታመናል። ሀገሪቱ ለዓለም በኪነ ጥበብ፣ በባህል፣ በተፈጥሮ፣ በኪነ ሕንፃና ስነ ፅሁፍ እውቀት ያበረከተች መሆኗም እሙን ነው። ለዚህ እንደ ጥሩ ማሳያ የሚሆኑት ቀደም ያሉ የስልጣኔ አሻራዎች ናቸው።

ኢትዮጵያ ለምድራችን የማይዳሰሱና የሚዳሰሱ በቅርስነት ተመዝግበው የሚገኙ ባህላዊ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶች፣ የስነ ፅሁፍ ውጤቶች፣ የዲሞክራሲ መገለጫዎችና ልዩ ልዩ እሴቶችን አበርክታለች። ሀገሪቷ ለመላው የሰው ልጆች ዛሬ ላይ የመድረስ ምክንያት እንደነበረች ህያው ምስክር የሆኑ ዛሬም በምሳሌነት የሚቀርቡ በርካታ ማስረጃዎችን ማንሳት ይቻላል።

ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነን ከትናንት በስቲያ በኦሮሞ ማህበረሰብ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው የአባ ገዳ ዲሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር መመልከት ይቻላል። የገዳ ሥርዓት በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ የነፃነት፣ የመከባበር፣ ታላላቆችን የማድመጥ እንዲሁም ህግና ህግጋቶችን ሳይተላለፉ የማክበር መገለጫ ተደርጎ የሚወሰድ እሴት እንደሆነ ያመለክተናል። የዝግጅት ክፍላችንም ይህንን ዲሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር በስፍራው ተገኝቶ የተከታተለ ሲሆን ሥርዓቱ በምን መልክ እንደሚከወንና ያሉትን እሴቶች እንደሚከተለው ዳሰሳ አድርጎበታል።

### የገዳ ሥርዓት- ዲሞክራሲያዊ ስልጣን ሽግግር

በኦሮሞ ባህል እና የታሪክ መሰረቶች ሲነሱ ሁሌም ገዳ እና የገዳ ሥርዓት አብሮት ይነሳል፡፡ በበርካቶች ዘንድ ገዳ እና ኦሮሙማ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው ተብለውም ይታሰባሉ። ይህንንም በርካታ ምሁራንና የታሪክ አጥኚዎች በተለያየ አውድ ገልፀውታል፡፡ የገዳ ሥርዓት ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ከሚደረግባቸውና በዓለማችን ከሚደነቁ ባህላዊ የአስተዳደር ሥርዓቶች አንዱ መሆኑ ይገለፃል። በሥርዓቱ መሰረት የአንድ አባ ገዳ ስልጣን ዘመን በስምንት ዓመት የተገደበ ሲሆን፤ ለቀጣዩ አባ ገዳ ስልጣን የሚሰጠው ደግሞ በመመራረቅ ነው። አንዳንድ ምሁራንም የዘመናዊ የዴሞክራሲ ጽንሰ ሃሳብ በግሪክ ፈላስፎች ሳይታወቅ የኦሮሞ ሕዝብ ዴሞክራሲን ይተገብር ነበር፤ በፍልስፍናውም የቀደመ ነው ሲሉም ያሞካሹል፡፡

ሰሞኑንም የጉጂ አባ ገዳዎች ላለፉት ስምንት ዓመታት ያገለገሉትን አባ ገዳ ጂሎ ማንዶ ለአገልግሎታቸው አመስግኖ አባ ገዳ ጃርሶ ኡጎ ለጉጂ ኦሮሞዎች 75ኛው አባ ገዳ አድርጎ የ‹‹ባሊ›› ስልጣን ርክክብ አድርጓል፡፡ ይህም በስልጣን ሽግግሩ ከሐርሙፋ አባገዳ ወደ ሮበሌ አባ ገዳ የስልጣን ሽግግር ተደርጓል ማለት ነው፡፡ በጉጂ ዞን አዶላ ከተማ አቅራቢያ ሚኤ ቦኮ አርዳ ጂላ በሚባለው ስፍራ በተከናወነው በዚህ መርሐ ግብር በርካታ ክንውኖችና ትዕይንቶችም ነበሩ፡፡

በቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ የሦስተኛ ዲግሪ ተማሪ የሆኑትና ለበርካታ ዓመታት የገዳ ሥርዓትን በተመለከተ ምርምር እያደረጉ ያሉት ደንቢ ቱርጬ እንደሚሉት፤ የገዳ ሥርዓቱ የኦሮሞ ሕዝብ የልብ ትርታ ሲሆን ዘመናትን ያሳለፈበት በመሆኑ ትልቅ ትርጉም ይሰጠዋል። ሰሞኑንም በ75ኛው የጉጂ አባ ገዳዎች የ‹‹ባሊ›› ስልጣን ርክክብ ላይ ያለው ሁነት ይህን ያሳያል፡፡ በሥርዓቱ መሰረት አንድ የጉጂ አባ ገዳ ከተመረጠ የስልጣን ዘመኑ በስምንት ዓመታት የተገደበ ነው፡፡ ይህ የተመረጠ አባ ገዳ ታዲያ አራቱን ዓመታት በመላው ጉጂ እየተንቀሳቀሰ ይመለከታል፣ በእኩል ዓይን ይዳኛል፣ ያስታርቃል፣ ስለ ገዳ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ የተረከበውን የጉጂ ወሰን ያከብራል፤ ያስከብራል፡፡ ዋነኛ ተልዕኮውም ሰላምና መረጋጋትን ማስፈን ነው፡፡ ቀሪዎቹን አራት ዓመታት ደግሞ በአንድ ቦታ ይቀመጣል፡፡ በዚህ ጊዜ የአስተዳደር ሥራውን እየሰራ ለቀጣይ አባገዳም አስቻይ መሰረትን አስቀምጦ ይሄዳል።አንድ አባ ገዳ እጅግ ከሚከፋባቸው ነገሮች መካከል በአስተዳደር ዘመኑ፤ ፀብ እና ጥላቻ ሲበረታ፣ ጦርነትና ቅያሜዎች ሲበራከቱ፣ ድርቅና ረሃብ የጠና እንደሆነ እጅግ ያሳስባቸዋል፡፡ አባ ገዳዎች ደስታቸው ሰላምና መረጋጋት ሲሆን፤ ለዚህ ሌት ተቀን አበክረው ይሠራሉ፡፡ በዚህ ላይ የጉጂ አባ ገዳዎች ብዙ እንደሰሩና እርሳቸውም ጥናቶችን እንዳደረጉ ይናገራሉ፡፡

አባ ገዳው ለሚቀጥሉት ስምንት ዓመታት በሚያስተዳድርበት ግዛት ውስጥ የተከበረ፣ የሚደመጥና የመወሰን አቅም ጭምር ያለው ነው። ማህበረሰቡም አባ ገዳዎች የደነገጉትን የመተላለፍ ልምድ የለውም፡፡ ለዚህም ሲባል ያገለግሉኛል ብሎ ስለሚያምን ለባህሉ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ አባ ገዳዎች ወደ ስልጣን የሚመጡት ስለፈለጉ ብቻ ሳይሆን ከልጅነት ስማቸው ጀምሮ በሥርዓቱ ሁሉም እርከኖች አልፈውና ተኮትኩተው አድገው ነው፡፡ በተለይም ደግሞ በሥራ ታታሪ እና ከራሱ አልፎ ለሌላው ማድረግ የሚችል የኢኮኖሚ አቅም፣ በማህበረሰቡ የተወደደና ተቀባይነት ያለው፣ ቤተሰቡም ጨምሮ በዕዳ እና ክስ የማይታወቁ ለሥርዓቱ ታማኝ እና ምስጢር ጠባቂ መሆን አለበት፡፡

አባ ገዳዎቹ በመጨረሻዎቹ የስልጣን ርክክብ ሂደትም ረጅምና ጥልቅ ነው የሚሉት ተመራማሪው፤ ብዙ ውጣ ውረዶች የሚታለፉ ይሆናል፡፡ በመጨረሻው የ‹‹ባሊ›› ስልጣን ርክክብ ሳምንት የሚሰነብቱበትን ጎጆ በሚኤ ቦኮ አርዳ ጂላ ይቀልሳሉ። ይህ ጎጆ ‹‹ቀጫ›› ይባላል፡፡ ይህ ቤት በተመረጡ ሰዎችን በተመረጠ እንጨት የሚሰራ ነው፡፡ ቀጫ ሲሰራ ወይንም መሰረቱ ወይንም የምሰሶ መቆሚያ ጉድጓ በማር፣ ቅቤ እና ወተት ይደፋበታል። ይህም ጉጂ ያለውን ሀብት ለማመላከት እና የበረከት መገለጫ ነው፡፡ አባ ገዳዎቹም በዚህ ቀጫ ውስጥ ሆነው የተለያዩ ሥርዓቶችን ይፈጽማሉ፡፡ ቀጫ ውስጥ ከተፈቀደላቸው ሰዎች ውጭ መሰስ ብሎ አይገባም፤ የተነወረ ነው፡፡ የአባገዳው ሚስት ‹‹ሀዳ ቦላ›› ከአባገዳው ያልተናነሰ ሚና ያላት ሲሆን ከቀጫ ውስጥ አብረው ይመክራሉ፡፡ በስልጣን ርክክብ ሂደት ደግሞ ዘርፈ ብዙ ትርጉም ያላቸው ሁነቶችም አሉ። ይህ የስልጣን ርክክብ የሚካሄድበት ስፍራ ልዩ ቦታ ተደርጎም ይወሰዳል፡፡ በዚህ አካባቢ የተነወሩ ድርጊቶችን መፈጸም የተከለከለ ነው። በዚህ ስፍራ መጣላት፣ ርግማን፣ ስርቆትና የመሳሰሉት ፈጽሞ የማይታሰቡ ናቸው፡፡

በጉጂ አባ ገዳዎች ሥርዓት መሠረት፤ ስልጣን አስረካቢው በማር፣ በቅቤ እና ወተት መግቦ እና በጋራ በልተው ነው ሽግግሩ የሚደረገው፡፡ ይህም ከልብ የሆነ መሰጠትን የሚገልጽ ሲሆን፤ ማር ቅቤ እና ወተቱ ደግሞ የበረከት፣ የሞልቶ መፍሰስ የመልካም ምኞት መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ከዚህ በዘለለ ግን በ‹‹ባሊ›› ርክክብ ሂደት ውስጥ ብዙ ጉዳዮች ለመገናኛ ብዙኃን ሆነ ለሕዝቡ ይፋ የማይደረጉ ነገር ግን አባ ገዳዎች ብቻ የሚፈጽሟቸው ሥርዓቶችም አሉ፡፡

በመጨረሻዎቹ የስልጣን ርክክብ ወቅት ግን ጉባዔው ‹‹ጉሚ›› በጋራ የወሰናቸው ድንጋጌዎች በተደጋጋሚ እና በስፋት ህብረተሰቡ እንዲያውቀው ይታወጃል። ለአብነትም የጉጂ አባ ገዳዎች ሰሞኑን በተደጋጋሚ ድንጋጌዎችን አሳውቀዋል፡፡ ይህን ድንጋጌም የሚናገሩት ህግ ደንጋጌዎች ወይንም ‹‹ዩባዎች›› ይባላሉ፡፡ ዩባዎች በገዳ ሥርዓት ውስጥ ድንጋጌዎች ለማሳወቅ ወይንም ለማስረጽ በተደጋጋሚ የአባ ገዳው የምክክር አባላት ወይንም ጉባኤ የወሰነው ይህ ነውና እወቁ ሲሉ ያሳስባሉ፡፡ ለአብነትም ሰሞኑን የጉጂ አባ ገዳዎች ሴትን በተመለከት፣ መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን በተመለከተ፣ ጋብቻን በተመለከተ፣ ሰላምና መረጋጋትን በተመለከተ ትኩረት አድርገውባቸው ከመከሩባቸው ጉዳዮችና በዩባዎች አማካይነት ለሰባት ቀናት ሲነገሩ የሰነቡት ናቸው፡፡ የደን ሀብትን በተመለከተ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ሲሆን፤ ሰማይ እና ምድር ከተፈጥሮ ጀምሮ አራዊቶች መጠለያቸው ደን ስለሆነ እነዚህን ማፈናቀል ከሰብዓዊነት አኳያም አግባብ አለመሆኑን ደጋግመው አሳውቀዋል፡፡

አባ ገዳዎች የወሰኑት ወይም የደነገጉትም የሚከበር መሆኑ ነው የሚሉት አቶ ደንቢ፤ በተለይም ደንን እና የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምን በተመለከተ የሚተላለፈው መልዕክት ህብረተሰቡ ይተገብረዋል። ደኑንም ያለ አግባብ አይመነጠርም፡፡ በዚህም የተነሳ የጉጂ ዞን እጅግ ከፍተኛ ጥቅጥቅ ያለ የደን ክምችት ያለበት ነው፡፡ ይህን ተላልፎ የተገኘም እስከ ስምንት የቀንድ ከብቶችን የሚቀጣ ይሆናል፡፡ ሴት ልጅን ያለ ፍላጎቷ ጋብቻ እንድትመሰርት ማድረግ፣ በትዳር ላይ መባለግና የመሳሰሉትም በገዳ ሥርዓት ውግዝ ነው፡፡ የጉጂ አባ ገዳዎችም ይህን በተመለከተ ከሁለት ቀንድ ከብት ጀምሮ እንደየጥፋቱ ሁኔታ ሌሎች ቅጣቶች እንደሚኖሩ ደንግገዋል፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሥልጣኑን የተረከበው አባ ገዳ ደግሞ በርካታ የቤት ሥራዎች ይሰጡታል፡፡ ቀደም ሲል የነበረው አባ ገዳ የጉጂ ወሰን ስለማስከበሩ፤ በተለያዩ ቦታዎች የነበሩ ግጭቶችን በሰላም ስለመፍታቱ ገዳ ሥርዓት የሚያዛቸውን ግዳጆች ስለመፈጸሙና ሌሎችን ጉዳዮች ያነሳል፡፡ በመጨረሻ ግን በእነዚህ የስልጣን ዘመን ያልተሳኩት እነዚህ ጉዳዮች ናቸው በማለት ለስልጣን ተረካቢው ያስረዳል። ይህም በገዳ ሥርዓት ጥንካሬን ብቻ ሳይሆን ጉድለቶችን ማመላከት አግባብ በመሆኑና ስልጣኑን የሚረከበው አባ ገዳ የበለጠ ተግቶ እንዲሰራ የሚያደርግ ነው፡፡ ስልጣን የተረከበው አባ ገዳም ከመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ‹‹ጉድለቶችን እንዴት ማስተካከል ይቻላል›› በሚለው ላይ በጥልቀት የሚመክር ሲሆን ጠንካራውን የበለጠ ለማጎልበት ይሰራል፡፡ በተጨማሪም ከስምንት ዓመት በኋላ ስልጣን ለሚረከበው አባ ገዳ አመቺ ሁኔታዎችን እየፈጠረ ይሄዳል፡፡

አቶ እያሱ በሳዬ በጉጂ ዞን የባህላዊ ፍርድ ቤት አባልና የታሪክ ተመራማሪ ሲሆኑ፤ በገዳ ሥርዓት አመጋገብም፣ ስጦታም ሆነ አለባበስ ፈርጅ አለው ይላሉ፡፡ አባ ገዳዎች ስለሚከበሩ አቅም በፈቀደ መጠን የአካባቢው ማህበረሰብ ለአባ ገዳዎች የሚሹትን ይሰጣሉ፡፡ ከሚበላ ምግብ ጀምሮ እስከ ሰንጋ በሬ በስጦታ መልክ የሚቀርቡ አሉ። ይህም ‹‹ጉማታ›› ይባላል፡፡ አባ ገዳዎችም ይህ አነሰ፤ ይሸኛው በዛ ሳይሉ መርቀው ይቀበላሉ፡፡ የዚህ ስጦታ ትልቁ ዓላማ አክብሮትን ለመግለፅ ጭምር ነው፡፡ ዋነኛ ምግባቸው ማር፣ ገንፎ፣ ቅቤ እና ወተት ብሎም ሥጋ ሌሎች የእንስሳት ተዋፅዎችን ነው፡፡ በመጠጥ ረገድ ደግሞ ‹‹ቦካ›› የማር ብርዝ ነው፡፡ ‹‹ቡና ቀላ›› ወይንም ድፍን ቡና ተቆልቶ እና በነጠረ ቅቤ ውስጥ ይጨመር እና ባህላዊ ብርጭቆ ወይንም ስኒ ውስጥ ይጨመራል፡፡ ይህ በጣም የተለመደ እና ዘወትር ማለዳ የሚዘወተር ነው፡፡ ይህን ምግብ ለማዘጋጀት ትልቁን ኃላፊነት የሚወስዱት እንስቶቹ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ሌሎች የምግብ ዓይነቶች የተለመዱ ናቸው፡፡ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ከስልጣን ማስረከብ ጀምሮ እስከ አመጋገብ ብሎም ስጦታ ማበርከት ያለው ሂደት ባህላዊ ይዘቱን ጠብቆ የሚሄድ ነው፡፡ በጉጂ አባ ገዳዎች ዘንድ የሚፈፀመው 75ኛው የ‹‹ባሊ›› ሥልጣን ርክክብ መርሐ ግብር በዚሁ መሰረት የተከናወነ ነው።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## የሀሮማያ ሐይቅ ትሩፋት

ስምስም መንግሥቱ

በምሥራቅ የኢትዮጵያ ክፍል ብቸኛ ሀይቅ እንደሆነ የሚነገርለት ሀሮማያ ሀይቅ ላለፉት 17 ዓመታት ደርቆ መቆየቱና አሁን ደግሞ መልሶ ካገገመ ወደ አራት ዓመት እንደሆነው ይታወቃል፡፡ ሀይቁ ወደ ቀድሞ ይዞቱ ሙሉ ለሙሉ እንዲመለስ ክትትሉና የምርምር ሥራው አሁንም እንደተጠናከረ ነው፡፡ ሀይቁ መልሶ ካገገመ ዓመታትን ቢያስቆጥርም የአካባቢው ነዋሪዎች ግን አሁንም መልሶ ይጠፋል የሚል ስጋት አላቸው ፡፡

ሁልጊዜም እየተመላለሱ ሀይቁን በስስት አይተው ይመለሳሉ፡፡ በጀልባ ለመዝናኛነት ውሎ ጎብኚዎችን እያስተናገደ፣ ከሀይቁ የወጣ አሣ እዛው ተጠብሶ ለጎብኚዎች እየቀረበ ይገኛል፡፡

ይህ ሁኔታ ቢያስደስታቸውም አሁንም ዓይናቸውን ከሃይቁ ላይ እንደማይነቅሉ ነው የአካባቢው ነዋሪዎች ያስረዱት፡፡ሀይቁ ጥቅም ባይሰጣቸውም ውሃውን በዓይናቸው ማየታቸው ብቻውን በቂ እንደሆነ ነው ነዋሪዎቹ የነገሩን፡፡

በነዋሪዎቹ እንዲህ ያለው ስሜት የተፈጠረው፤ ሐሮማያ ሀይቅ በማይገመት ሁኔታ ደርቆ ለ17 ዓመታት መቆየቱ በብዙዎች ዘንድ ድንጋጤን በመፍጠሩ ነው፡፡ የተፈጠረው ነገር አገግሞ መልሶ ሀይቅ ሆኖ ለማየት ተስፋ የሚሰጥም አልነበረም፡፡ ሀይቁ ደርቆ የእግረኛ መንገድና ለከብቶች ግጦሽ እስከመዋል ደርሶ ነበር፡፡አሁን ዳግም ማገገሙ በብዙዎች ዘንድ ግርምትን ፈጥሯል፡፡

አንዳንዶችም ስለሀይቁ መመለስ ስሜታቸውን መቆጣጠር እስኪያቅጣቸው እምባ እየተናነቃቸው ነበር አስተያየት የሰጡን። ነዋሪዎቹ እንዳሉት ሀይቁ ብዙ ነገራቸው ነበር፡፡ ልብሳቸውን ያጥባሉ፣ ንጽህናቸውን ይጠብቁበታል፣ የአሣ ሀብት የሚገኝበት በመሆኑም የኢኮኖሚ ምንጫቸውም ነበር። ላለፉት 17 ዓመታት ያጡት ይሄን ብቻ አልነበረም፡፡

ሀይቁ ዳር ሄደው በመዝናናት የሚያሳልፉት የደስታ ጊዜም ጭምር ነበር፡፡ የአካባቢ ስነምህዳር በመጠበቅ ባለው አስተዋጽኦም ንጹህ አየር አጥተው ቆይተዋል፡፡ የዓይናቸው ማረፊያም በመሆኑ የሀይቁ መድረቅ በአካባቢው ማህበረሰብ ስነ ልቦና ላይ ያሳደረው ተጽእኖ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም፡፡ ተስፋ ቆርጠው አሁን ደግሞ አገግሞ መልሰው ለማየት መቻላቸው ነው በደስታ ሲቃ ስሜታቸውን እንዲገልጹ ያደረጋቸው፡፡

ሀይቁ ሲመለስ የአካባቢው ነዋሪ የደስታ ስሜት ከሚገለጸው በላይ ነበር፡፡ የአካባቢው ነዋሪ አቶ ረመዳን አሊ ሀጂ፤ ሀረማያ ሀይቅ ከመድረቁ በፊት ስለነበረው ይዞታም ሆነ ከደረቀ በኋላም ስለነበረው ጉዳት፣ አሁን ደግሞ መልሶ ሲያገግም በስፍራው ነበሩ፡፡

አቶ ረመዳን፤ በቁጭትና በደስታ ስሜት ውስጥ ሆነው ነበር ሃሳባቸውን ያካፈሉን። በተለይም ሀይቁ ደርቆ በነበረበት ወቅት የተሰማቸውን ከፍተኛ ሀዘን ሲያስታውሱ፤ አሁንም እምባ ይቀድማቸዋል፡፡ ሀይቁ መመለሱ መግለጽ ከሚችሉት በላይ ደስታም ተሰምቷቸዋል፡፡

ሀይቁን አሁን የበለጠ በስስት እንደሚያዩትና ሀይቁን ከብክለት ለመከላከልም በየቀኑ ዙሪያውን በማጽዳት፣ በመንከባከብ በኃላፊነት እየሰሩ እንደሆነም ነግረውናል፡፡ በተለያየ ሥራ በአካባበው ላይ በመንቀሳቀስ ተጠቃሚ የሆኑ ታዳጊዎችንና ወጣቶችን በማስተባበር በጋራ እየተጠቀሙ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡

ሀይቁ በሚገኝበት ስፍራ ተወልዶ ማደጉን የነገረን ወጣት ፋሲካ ሰለሞንም ሀይቁ ደርቆ በነበረበት ጊዜ እጅግ በጣም አዝኖ እንደነበርና መልሶ ሲያገግምም ደስታው ከሚገልጸው በላይ



መሆኑን ይናገራል፡፡ ወጣት ፋሲካ አሁንም መልሶ እንዳይደርቅ ስጋት አለው፡፡ በውስጡ የሚገኘው ቆጠማ መጽዳት እንዳለበትና የሀይቁ የውሃ መጠን እንዲጨምር ገባሮች እንደሚያስፈልጉ አስተያየት ሰጥቷል፡፡

ሀይቁን ለማየት ከቅርብም ከሩቅም ጎብኚዎች ወደ ስፍራው ይመጣሉ፡፡ ከፊሉ በሀይቁ ዳር ሆኖ በእይታ ተዝናንቶ የሚመለስ ሲሆን፤ አንዳንዱም ከሀይቁ ተጠምዶ ወዲያው ተጠብሶ የሚቀርብ አሣን እያጣጣመ፣ ሻይ ቡናም እያለ፣ በሀይቁ ውበት ይደመማል፡፡

በጀልባ በሀይቁ ላይ እየተዝናኑ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉ እንግዶችንም አይተናል፡፡ የሀይቁ ማገገም እነዚህን ጥቅሞች ከማስገኘቱ በተጨማሪ የአካባቢ ሥነምህዳር እንዲስተካከል አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም ለአካባቢው ታዳጊዎች፣ ወጣቶችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል የኢኮኖሚ ምንጭ መሆን ጀምሯል፡፡ በአካባቢው በመለስተኛ አገልግሎት ሻይ ቡና በማቅረብ፣ እንዲሁም የጀልባ አገልግሎት በመስጠት ይጠቀማሉ፡፡ በዚህ ተጠቃሚ የሆኑትም አብዛኞቹ ታዳጊዎችና ወጣቶች ናቸው፡፡


በጀልባ አገልግሎት ሲሰጡ ካገኘናቸው ታዳጊዎች ‹‹እኔ የጀልባ ሾፌር ነኝ›› በማለት እራሱን ያስተዋወቀን ታዳጊ ሐምዛ ፎዚ፤ ስለሀሮማያ ሀይቅ ሲነገር እንጂ ታሪኩን በደንብ እንደማያውቅ ነው የገለጸልን፡፡ አሁን ግን ጥቅም እያገኘበት እንደሆነ ነግሮናል፡፡

ታዳጊው እንደገለጸልን፤ አገልግሎት የሚሰጥበት ጀልባ ባለቤቱ ሌላ ሰው ነው። ባለቤቱ ለሰራበት ክፍያ ያስብለታል፡፡ ክፍያ የሚያገኘውም እንደስራው ሁኔታ ነው፡፡ በቀን የሚያገኘው ሁለት መቶ ብርም ከዚያም በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ በሚያገኘው ክፍያም ተጠቃሚ ሆኗል፡፡ ተማሪ በመሆኑ ለትምህርት ቤት የሚያስፈልገውን ለማሟላት ቤተሰብ አያስቸግርም፡፡ በራሱ ያሟላል፡፡ ቤተሰቡም በአነስተኛ ገቢ የሚተዳደሩ በመሆናቸው ከሚያገኘው ክፍያ ይደጉማል፡፡

ታዳጊ ሐምዛ ለጎብኚዎች የጀልባ አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ ከተሰማራ አንድ ዓመት ሆኖታል፡፡ እስካሁንም በተለያየ መንገድ ተጠቃሚ እንደሆነ ይናገራል፡፡ አገልግሎቱን የሚሰጠውም ከትምህርት ቤት መልስ በሚኖረው ትርፍ ጊዜ ነው ፡፡ አንዳንድ የእድሜ እኩዮቹ ከትምህርት ቤት መልስ የሚያሳልፉባቸው ቦታዎች ለእድሜያቸው የሚመጥን አይደለም፡፡

በሀይቁ የጀልባ አገልግሎት በመስጠት ማሳለፉ ያልሆነ ቦታ እንዳይውል ጠቅሞታል፡፡ ሥራ ሰርቶ፣ ጥሩ ነገርም አይቶ፣ ገንዘብም አግኝቶ ነው ጊዜውን በአግባቡ እንዲጠቀም አድርጎታል።

ለጉብኝት ከሚመጡት ሰዎች በተጨማሪ ከሀሮማያ ዩኒቨርሲቲና ከተለያዩ ተቋማት በሀይቁ



ላይ ሥራ የሚሰሩ ሰዎች በስፍራው እንደሚገኙና ከነዚህ ሰዎች ጋር በመዋሉም አንዳንድ ግንዛቤዎችን ለማግኘት አስችሎታል፡፡ ደስተኛ እንደሆነና ወደፊት የራሱ ጀልባ ኖሮት እራሱን ችሎ እንደሚሰራም ተስፋ አድርጓል፡፡

በሀይቁ ላይ በጀልባ በመሄድ በአካባቢው ጊዜያቸውን ለማሳለፍ ወደ ስፍራው የሚሄዱት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ቢሆኑም፤ በቡድንም በተናጠልም ወደ ስፍራው የሚሄዱ ወጣቶች ይበዛሉ፡፡ በተለየ ሁኔታ ያላቸውን ስሜትም በወቅቱ በስፍራው ያገኘናቸውን ወጣቶች ጠይቀናል፡፡

ካነጋገርናቸው ወጣቶች በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ የሆነው ወጣት ባጫ አበራ ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ ነበር ሐይቁን ለመጎብኘትና በጀልባም ለመዝናናት በስፍራው የተገኙት፡፡ እርሱ እንዳለው ወደ ሀይቁ ሲሄዱ የመጀመሪያቸው ነው፡፡

ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ ተመድቦ መማር እስኪጀምር ድረስ ስለሀይቁ ታሪክ መረጃው አልነበረውም፡፡ ዝናውን ከሰማ በኋላ ግን ሀይቁን ለማየት ጉጉት አደረበት፡፡ በትምህርቱና በተለያየ ምክንያት ሀይቁን ቶሎ ባያየውም አንድ ቀን እንደሚያየው ግን እርግጠኛ ነበር፡፡ ጊዜው ደርሶ ከጓደኞቹ ጋር ሀይቁን ለመጎብኘት ችሏል፡፡

ወጣት ባጫ በሀይቁ ላይ ስለነበረው ቆይታም እንደተናገረው፤ ጊዜውን ከጓደኞቹ ጋር በጥሩ ሁኔታ አሳልፏል፡፡ በትምህርት ላይ የቆየውን አእምሮውንም ዘና አድርጓል፡፡ እንዲህ አእምሮውን አድሶ ሲመለስ ትምህረቱን በጥሩ አእምሮ ለመቀበል ያስችለዋል፡፡

ስለሀይቁ በሰማው ታሪክም ‹‹ሀይቁ እንደደረቀ ቀርቶ ቢሆን ኖሮ እኔም ጓደኞቼም በዚህ ስፍራ ተገኝተን አንዝናናም ነበር፡፡ ታሪኩንም ለማወቅ እድሉ አይኖረንም ነበር፡፡ ሀይቁ መልሶ ማገገሙ እኛንም ጠቅሞናል›› ሲልም ተናግሯል፡፡

ወጣት ባጫ፤ ሀይቁ ዳግመኛ ለመድረቅ ለስጋት እንዳይጋለጥ መንከባከን ያስፈልጋል፡፡

በሀይቁ አካባቢ ለወጣቶች ስለተፈጠረው የሥራ እድል በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ የሀሮማያ ሀይቅ ተፋሰስ ልማት ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ ዲኔ ረሽድ እንደገለጹልን ፤ሀይቁ ከተመለሰ ወዲህ ያለበትን ሁኔታ ለማየት ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ ሰዎች ቁጥር በየቀኑ እየጨመረ ነው፡፡ በዓመትም በአማካይ እስከ 50ሺ ሰዎች ይጎበኙታል፡፡ ወደ ቱሪስት መስህብነት እየተቀየረ ይገኛል፡፡

ይህን ተከትሎም ለአካባቢው ወጣቶች የገቢ ምንጭ መሆን ጀምሯል፡፡ በማህበር ተደራጅተው የተለያየ አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ ሀይቁ መልሶ ማገገሙ ለአካባቢው ማህበረሰብ የኢኮኖሚ ምንጭ መሆን ችሏል፡፡

ምንም እንኳን የዩኒቨርሲቲው ዋና ትኩረት ሀይቁ ዘላቂ በሆነ መልኩ ማቆየት ቢሆንም ሀይቁ የቱሪስት መዳረሻ እንዲሆን የአካባቢው አስተዳደር ትኩረት አድርጎ ቢሰራበት ወደፊት ለአካባቢው ነዋሪዎች ሰፊ የሥራ እድል ከመፍጠር በተጨማሪ የአካባቢውን ኢኮኖሚ ለማነቃቃት ያግዛል፡፡

አካባቢው የቱሪስት መዳረሻ ሆኖ ጥቅም እንዲሰጥ ሀይቁን ከጉዳት መጠበቅ ይገባል ያሉት አቶ ዲኔ፤ የሥራ እድል የተፈጠረላቸውም ሆኑ ጎብኚዎች በሀይቁ ላይ ጉዳት የሚያስከትል ነገር እንዳያደርጉ የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት ክትትል እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡ የአካባቢውን ማህበረሰብ በማስተባበርም የጽዳት ዘመቻ ሥራ እየተከናወነ እንደሆነም ገልጸዋል፡፡ ወደ ሀይቁ ቆሻሻ እንዳይገባ ለመከላከል የሚያስችሉ የግንባታ ሥራዎች እንደሚከናወኑ ተናግረዋል፡፡

ሀይቁ በአሁኑ ጊዜ ስለሚገኝበትና እየተከናወኑ ስላሉ ተግባራትም አቶ ዲኔ እንዳብራሩት፤ ለሀይቁ መልሶ ማገገም የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፡፡ ዩኒቨርሲቲው የተቀናጀ የሀሮማያ ሀይቅ ተፋሰስ ፕሮጀክት ቀርጾ በደን መመናመን የተራቆቱ አካባቢዎችን በተለይም በሀይቁ ዙሪያ ባሉ ተራራማ አካባቢዎች የዛፍ ችግኞችን በመትከል፣ በአፈርና ጥበቃ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

በዚህ በተከናወኑት ተግባራትም ባለፉት አራት ዓመታት ጥሩ የዝናብ ሽፋን ማግኘት በመቻሉ ለሀይቁ መልሶ ማገገም ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

የሀይቁ የውሃ መጠንም ከዓመት ዓመት መሻሻል እያሳየ መሆኑን የተናገሩት አቶ ዲኔ፣ በየጊዜው ክትትል እንደሚደረግና መረጃም እንደሚሰበሰብ ገልጸዋል፡፡ እርሳቸው እንዳሉት የሀይቁ ጥልቀት በአማካይ ወደ አራት ሜትር ሲሆን፣ ዙሪያው ደግሞ ወደ 226 ሄክታር ይሆናል፡፡

# የምድር በረከት

## የማዕድን ሀብትን የሀገር ኢኮኖሚ አውታር የማድረጉ ጥረት

**ማህሌት አብዱል**

ኢትዮጵያ በርካታ የማዕድናት ሀብት ካላቸው የአፍሪካ ሀገራት አንዷ እንደሆነች ይታወቃል። በተለይም ወርቅና ፕላቲኒየም የመሳሰሉ የከበሩ ማዕድናት መገኛ እንደሆነች ይጠቀሳል። ከወርቅና የከበሩ ማዕድናት ተጨማሪ ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ማዕድናት በስፋት ይገኛሉ፡፡ ፖታሽ፣ ኖራ፣ የድንጋይ ከሰል፣ ታንታላይት፣ ፌልድስፖር፣ ኳርትዝ፣ ዶሎማይት ያሉ የኢንዱስትሪ ማዕድናት በተለያዩ ክልሎች እንደሚገኙ በጥናት ተረጋግጧል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንደ ብረትና የድንጋይ ከሰል የመሳሰሉ ለኢንዱስትሪ ልማት ዋነኛ ግብዓት የሆኑ ማዕድናት በስፋት እየተገኙባት እንደሆነ ይነገራል። እነዚህ ማዕድናት ታድያ በስፋት ከሚገኙባቸው አካባቢዎች መካከልም ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ዋነኛው ተጠቃሽ ነው። ሱማሌና አፋር እንዲሁም ሌሎችም ክልሎች ላይ መጠናቸው ይለያይ እንጂ በዓለም ገበያ እጅግ ተፈላጊ የሆኑ በርካታ የማዕድን ሀብቶች ይገኛሉ።

በአንዳንድ አካባቢዎች ሰፊ የማዕድን ሀብት ስለመኖሩ ለዘመናት በአካባቢው ማህበረሰብ ቢታወቅም በተጨባጭ በሳይንሳዊ መንገድ ጥናት በማድረግ መጠኑና አይነቱን ለይቶ ለሀገር ጥቅም ማዋል ላይ ሰፊ ክፍተት ይታያል፡፡ ይልቁንም ማህበረሰቡ በራሱ ባህላዊ የአመራረት ሂደት ማዕድን እያወጣ የተለያዩ ቁሳቁስ በማውጣት ለዘመናት የቆየ ታሪክ እንደሆነ ይታወቃል። መረጃዎች እንደሚያሳዩትም ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የሀገሪቱ ዜጎች በባህላዊ ማዕድን ምርት የተሰማሩ ሲሆን፤ አብዛኞቹ የሚያመርቱት ወርቅ ነው፤ በአንዳንድ አካባቢዎችም እንደ ኦፓል ያሉ የጌጣጌጥ ማዕድናት እንዲሁም የኢንዱስትሪ አለኝታ እንደሆነ የሚጠቀስለት የብረት ማዕድን በተወሰነ ደረጃ በማውጣት እያለሙ የሚጠቀሙ እንዳሉም በተለያዩ ጊዜያት የሚወጡት መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

ይሁንና ታዲያ የእነዚህ ማዕድናት መጠን በውል የማይታወቁ አይደሉም፡፡ ለዚህም ማዕድናቱ በአብዛኛው በባህላዊ መንገድ የሚወጡና የማውጣት ሂደቱም ሳይንሳዊ መንገድን ያልተከተለ መሆኑ ዋናው ምክንያት ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ታዲያ ጥቅም ላይ ከሚውለው ማዕድን ይልቅ ለብክነትና ለህገወጥ ንግድ የሚዳረገው እጅጉን የሚልቅ እንደሆነ የዘርፉ ምሁራን ያነሳሉ፡፡ የሀገሪቱ ዋነኛ የውጪ ንግድ የሆነው የወርቅ ምርት እንኳን ዛሬም ድረስ ከሚድሮክ ጎልድ በስተቀር ዘመኑን በሚዋጅ የአመራረት ሂደትን እየተከተለ አይደለም። ይህም ሀገሪቱ ከዘርፉ ልታገኝ የሚገባትን ገቢ ዝቅተኛ ያደረገ መሆኑ የዘርፉ ተዋናዮች የሁልጊዜም ቁጭት ሆኖ ቆይቷል፡፡ ከዘርፉ ተዋናዮች ባለፈም ሀገርና ሕዝብ ከዘርፉ መጠቀም የሚገባቸውን ጥቅም እያገኙ አይደለም፡፡

በሌላ በኩልም ኢትዮጵያ በከርሰ ምድሯ ተፈጥሮ የለገሳትን የኢንዱስትሪ ግብዓት ማዕድናት አውጥታ መጠቀም ባለመቻሏ፣ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በማውጣት ከውጭ የተለያዩ ምርቶችን ታስገባለች፡፡ ለአብነት ያህል እንኳን ብንጠቅስ ሲሊካ የተባለ ለመስታወትና ጠርሙስ ማምረቻ የሚሆን ማዕድን በስምጥ ሸለቆ ውስጥ በብዛት ቢገኝም በስፋት ጥቅም ላይ ባለመዋሉ የመስታወት፣ ብርጭቆና ጠርሙስ ምርቶች በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከውጭ እየገቡ ይገኛሉ፡፡ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፣ ብርጭቆና ጠርሙስ ለማውጣት በውጭ ምንዛሪ በዓመት ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ



ይደረጋል፡፡

የቴክኖሎጂ አቅርቦት ዝቅተኛ መሆን፣ ለአምራቾች የሚደረገው የፋይናንስ፣ የቴክኒክና የአቅም ግንባታ ድጋፍ አነስተኛ መሆን ለዘርፉ ያለማደግ ምክንያት ተብለው ከሚጠቀሱ ችግሮች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በዘርፉ ያለው የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ አሰራር ደካማ መሆኑ የዘርፉ ዋነኛ ማነቆዎች እንደሆኑ ይነገራል፡፡ ህገወጥ የማዕድን ምርቶች በተለይም የወርቅ ንግድ መስፋፋት፣ ምርቶች ላይ እሴት ጨምሮ አለመላክ፣ መንግሥት በዘርፉ የሚሰጠውን ድጋፍና ማበረታቻ ተግባራዊ አለማድረጉ ሌሎች ቁልፍ ችግሮች ናቸው።

ከዚህም ባሻገር በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢ ዎች የነዳጅ ሀብት ስለመኖሩ በመንግሥትም ሆነ በዘርፉ ተወናዮች ሲነገር ይደመጣል፡፡ ይሁንና የማዕድንና ነዳጅ ፍለጋ ሥራ ከፍተኛ መዋእለ ነዋይ የሚጠይቅ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በኢኮኖሚና በቴክኖሎጂ ወደኋላ የቀሩ ሀገራት በመንግሥት በጀት ለመሥራት የሚታሰብ ባለመሆኑ ሀብቱ ጥቅም ላይ አልዋለም፤ በዚህ ምክንያትም ሀገሪቱ ዛሬም ከውጭ ሀገራት ጥገኝነት መላቀቅ አልቻለችም። በእርግጥ በተለያዩ ጊዜያት የነዳጅ ፍለጋና ማውጣቱን ሥራ ለመስራት የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መምጣታቸው ይታወቃል፤ ሆኖም በፀጥታና በተለያዩ ችግሮች የተጀመሩ ሥራዎች በብዛት ሲቋረጡ ይስተዋላል፡፡

በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተከሰቱ ግጭቶች አጠቃላይ የማዕድን ልማት ሥራው በከፊልና ሙሉ ለሙሉ የሚቋረጥበት ሁኔታ አጋጥሟል። በተጨማሪም ግርግር ለሌባ ይመቻል እንዲሉ በሀገሪቱ የተከሰተውን አለመረጋጋት ተገን በማድረግ የሕዝብና የሀገር ሀብት የሆኑ ማዕድናት በህገወጥ መንገድ እየወጡና እየተሸጡ የህገወጥ ግለሰቦች ኪስ እያዳበሩ መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ከሆነ ሰንበትበት ብሏል፡፡

መንግሥት ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ በዘርፉ የሚስተዋሉትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች መፍታት ያስችሉኛል ያላቸውን የተለያዩ የልማት ስትራቴጂዎች ነድፎ በመስራት ላይ ይገኛል። በተለይም ከአምስቱ የኢኮኖሚ ልማት ቁልፍ ተግባራት (ፒላሮች) አንዱ በማድረግ የማዕድን ልማት ዘርፉ ለሀገር እድገት ወሳኝ ሚና እንዲጫወት ርብርብ እያደረገ ስለመሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቅርቡ ሪፖርት ሲያደርጉ ተደምጠዋል፡፡ እንደ እርሳቸው ገለፃ፤ አሁን ባለው የሀገሪቱ ፖሊሲ ማዕቀፍ መሰረት ድረስ የሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ዘርፍ የኢኮኖሚው የጀርባ አጥንት እንዲሆን ታቅዷል፡፡

ምሁራን እንደሚገልፁት፤ ደግሞ ይህ የመንግሥት ትልም ሊሳካና የማዕድን ዘርፍ ልማት ውጤት ሊያመጣ የሚችለው በመለስተኛ የዕድገት አቅጣጫ የረዥም ጊዜ እቅድ ሲቀረፅ ነው፡፡ በማዕድን ዘርፍ ልማት ለመጠቀም፣ አሁን የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ፣ የማዕድን ፍለጋና የማዕድን ማውጣት የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበት ግልፅ ፖሊሲ፤ ህጎችና ደንቦች ማስቀመጥ ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪም የማዕድን ሚኒስቴር ተቋማዊ አቅም መገንባት፣ የተቆጣጣሪ ተቋማትን የአቅም ውስንነት ከግምት በማስገባት የማዕድን አልሚ ኩባንያዎችን በዘርፉ ንቁ ተሳታፊ ማድረግ ይገባል፡፡

ከዚህም ባሻገር ኢኮሎጂካዊ አዋጭ ስለሚባሉ አካባቢዎች በቂ መረጃ ማቅረብ፣ የማዕድን ገቢ ክፍፍል ሥርዓትን መቅረጽ ዘርፉን የሚያንቀሳቅሱ የመንግሥት ተቋማት ቀጣይ የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል፡፡ በረዥም ጊዜ ከፍተኛ የማዕድን ዘርፍ ከመፍጠር አኳያ፣ ፖሊሲ አውጪዎች ከዘርፉ የሚገኝን ጥቅም በበለጠ ማሳደግ የሚችሉበትን ዕቅድ ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም በዘርፉ ልማት የተገኙ ውጤቶችን የእሴት ሰንሰለቶች ለመፍጠር ማበረታታት የግድ ይላል፡፡

በሌላ በኩል ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ ዋና ዋና ማዕድናት የምርት አቅርቦትና ግብይት ላይ ያሉ መሰረታዊ ችግሮች፣ የመፍትሔ አቅጫዎች እና የባለድርሻ አካላት ሚና በመለየት ዘርፉ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ለማድረግ እየሰራ ስለመሆኑ መንግሥት በተደጋጋሚ ሲገልፅ ይደመጣል። የዘርፉ ተዋናዮች በበኩላቸው ግን መንግሥት እያደረገ ያለው ድጋፍ፣ ክትትልና ዘርፉ ካለው እምቅ አቅምና ከሚያስገኘው ገቢ አንጻር በመረዳት የሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑን ያነሳሉ። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ያለው የህገ ወጥ የማዕድን ምርቶች ንግድ በህጋዊ መንገድ የሚሰሩ አካላት ላይ ጉዳት እያደረሰ መሆኑንና መንግሥትም የተለየ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ያሳስባሉ። በዚህ ረገድ በተደጋጋሚ በማዕድኑ ዘርፍ ስላሉ ችግሮች ውይይት ቢደረግም የሚመለከታቸው አካላትም በጉዳዩ ላይ መፍትሄ በመስጠት እርምጃ ሲወስዱ ግን እንደማይታይ ያመለክታሉ።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በዘርፉ ተዋናዮች የሚነሱ ችግሮችን በሚመለከት የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የኤክስፖርት አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢና የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማይክሮ ኢኮኖሚ አማካሪ አምባሳደር ግርማ ብሩ የዘርፉ ተዋናዮችን ባነጋገሩበት ወቅት እንደገለፁት፤ መንግሥት ከዚህ በፊት ትኩረት ያልተሰጠውን የማዕድኑን ዘርፍ ትኩረት እንዲያገኝ ወስኗል። ከህገ ወጥ ማዕድን ምርትና ሽያጭ በተለይም ከወርቅ ግብይት አንጻር የሚነሱ ተግዳሮቶች በጥልቀት የችግሩን ምንጭ መተንተን እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

በዚህም ረገድ አስፈላጊው ሥራ በመንግሥት በኩል እንደሚከወን የጠቀሱት አምባሳደር ግርማ፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት በኩል የማዕድን ዘርፉን ችግሮች መፍታት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የሚሰራ አምስት አባላት ያሉት ግብረ ኃይል መቋቋሙንም ጠቁመውም ነበር። በዘርፉ የሚነሱትን ችግሮች በዝርዝር ጥልቅ ውይይት እንደሚካሄድባቸውና ከፖሊሲና ከአሰራር አኳያ እንዲሁም መንግሥት ምን አይነት ድጋፍ ማድረግ አለበት? በሚለው ዙሪያ ዝርዝር የመፍትሄ ሃሳቦች እንደሚቀርቡም ማመልከታቸው ይታወሳል።

እንደተባለው የማዕድን ዘርፉ ለሀገር እድገት ሁነኛ አቅም ይሆን ዘንድ በተለይም የመንግሥት፤ ማህበረሰቡና አልሚዎች ቅንጅት አሰራር ማጠናከር ወሳኝ ሚና አለው፡፡ ከዚህም ባሻገር ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽ ማድረግ፣ ምርቶች ላይ እሴት ጨምሮ መላክ፣ ህገ ወጥ ግብይትን ለመከላከልና እሴት መጨመር ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ላይ መንግሥት ሰፊ የቤት ሥራ እንዳለበት ይታመናል።

በዘርፉ ካለው እምቅ አቅም አኳያ በሥራ እድል ፈጠራም የላቀ ሚና እንዲጫወት ማድረጉ ላይ ትኩረት መደረግ እንዳለበት አጠያያቂ ጉዳይ አይደለም፡፡ እንዲሁም ባህላዊ ወርቅ አምራቾችን በማህበር፣ በአነስተኛና ጥቃቅን ማደራጀት፣ ዘመናዊ የአመራረት ዘይቤ እንዲጠቀሙ ሥልጠና መስጠትና የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን በማመቻቸት መንግሥት ወረዳና ቀበሌ ድረስ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይገባዋል። ይህ ብቻ ሳይሆን ባህላዊ አምራቾች ያሉባቸውን ችግሮች በጥልቀት በማጥናት ችግሮቻቸውን መፍታት ይጠበቃል፡፡ በእርግጥም ኢትዮጵያ ላሰበችው የአስር ዓመት የኢኮኖሚ ልማት መርሀ ግብር እውን መሆን እነዚህ ድምርና የጋራ የቤት ሥራዎችን መከወን ለነገ የሚተው ተግባር አይደለም፡፡

**መዝናኛ**

# የብዕር ጠብታ

## የትዝታ ገጾች

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ከአስር አመት በኋላ መኝታ ክፍሌ አልጋ ውስጥ ያስቀመጥኩትን የወረቀት ፋይል አገላብጣለሁ። ዩኒቨርሲቲ እያለሁ የማነባቸውን መጽሐፍቶች፣ የተማርኩባቸውን አንዳንድ ደብተሮች እያየሁ የትዝታ አለንጋ ገረፈኝ። ከዩኒቨርሲቲ ከወጣው ጀምሮ እጄን ወደ አልጋዬ ሰድጄ አላውቅም። ዛሬ ምን ወደዚያ እንደሰደደኝ አላውቅም...ትዝታዎቼ በአእምሮዬ ውስጥ እንጂ እንዲህ አካል ለብሰው ወረቀት ላይ አገኛቸዋለሁ ብዬ አልገመትኩም ነበር። አልጋዬ ስር ባስቀመጥኩት ትናንቴ ወደ ተውኩት አምና ተሰደድኩ።

የትዝታ ተጠቂ ነኝ...ትናንትና ምንም ይሁን ከነግሳንግሱ ይናፍቀኛል። ነገ የትናንትን ያክል ናፍቆኝ አያውቅም። ዘንድሮ ያምናን ያክል ብርቅ ሆኖብኝ አያውቅም። በእኔ ሕይወት ውስጥ ዛሬ ነገ ሲሆን ሁሉም ትዝታ ነው። ከሙዓለ ሕፃናት አሁን እስካለሁበት ጊዜ ድረስ ያለው ትናንት፣ ያለው አምና፣ ያለው ድሮ ናፍቆቴ ነው። ትናንትን አንቆ መግደል አቅቶኛል።

ብዙ ነገሮችን አየሁ...የረሳኋቸውን ብዙ ነገሮች አስታወስኩ። ደብተሬ ላይ የብዙ ጓደኞቼ የእጅ ጽሑፍ ነበር። ክፍል ውስጥ ማድመጥ እንጂ መጻፍ አልወድም ነበር፣ ለዚህም ክፍል ውስጥ እኔ ደብተር ላይ ያልጻፈ አንድም ተማሪ አልነበረም። ትናንትናዬን ገለጥኩት..ዛሬም ድረስ የማይረሳኝን የመክሊትን የእጅ ጽሑፍ ደረስኩበት። መክሊት የክፍላችን ብቻ አይደለችም የዩኒቨርሲቲያችን ብቸኛ ቆንጆ ተማሪ ነበረች። ዛሬም ድረስ የእሷን ዓይነት ቆንጆ ሴት አላየሁም። ድሮዊንግ አስተማሪያችን በእሷ ምክንያት ‹ኤፍ› እስከሰጠኝ ጊዜ ድረስ ተለያይተን አናውቅም ነበር።

አይ ትቸር ሞገስ...ትቸር ሞገስ ድሮዊንግ አስተማሪያችን ነው...ክላስ እንደገባ የመጀመሪያ ሥራው ወዳለችበት ተራምዶ አጠገቧ መቆም ነው። ከዚያ በኋላ ነው ብላክ ቦርዱ ላይ የሆነ ነገር ስሎ የሚያስተምረን። ከእኔ ኋላ ስለምትቀመጥ አጠገቧ ሲቆም ጥላው ያርፍብኛል። ዛሬም ድረስ የሚጠረንፈኝ ሽቶው ይሸተኛል። ሰማይ የተደፋብኝ ያክል ክብድ ይለኛል። ወንድነቱ ነፍሴ ላይ ያርፋል። ሰው እንዴት ያንን ያክል ይገዝፋል? ሳይናገር፣ ሳያወራ፣ ቃል ከአፉ ሳያወጣ የኔን ነፍስ ያስጨንቃታል። እሱ ጎልያድን እኔ ደግሞ ዳዊትን ሆነን እዚያ ስፍራ ለአንድ አመት ተሰቃይቻለሁ። ከአጠገቤ እብስ ሲል እንደ ዳዊት በጠጠር ያባረርኩት ነው የሚመስለኝ። በነጋታው አጠገቤ ጥላው አርፎብኝ ሳየው ጎልያድ ፊት እንደ ቆመው ኮሳሳው ዳዊት እኮስሳለሁ።

ትቸር ሞገስ የመክሊትን ስም ሳይጠራ አስተምሮን አያውቅም። ዛሬም ድረስ ያልገባኝ ነገር የሴት ስም ለአንድ ድሮዊንግ ምሳሌ ሆኖ መቅረቡ ነው። አመት ሲያስተምረን ከመክሊት ስም ሌላ ምሳሌ ተጠቅሞ አያውቅም። እኛ ክላስ ኤክስና ዋይ የሚያርፉት በድሮዊንግ ክላስ በመክሊት ስም ነው። ኤክስና ዋይ ነፍስ ቢኖራቸው ኖሮ መክሊትን የሚያመሰግኑ ይመስለኛል። ክላስ ውስጥ በእሷ ምክንያት ለሰባት ልጆች ‹ኤፍ› ሰጥቷል..ከዚያ ውስጥ አንዱ እኔ ነኝ። በአንድ ቆንጆ ሴት ምክንያት ምንም የማናውቅ የሰባት ወንዶች ህልም መደናቀፉ ዛሬም ድረስ ያናድደኛል። ትቸር ሞገስ ለምን መምህር እንደሆነ አላውቅም...

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መክሊትን ፈራኋት....ግዝት እንዳለበት ሰው በመቶ ሜትር ነበር የምርቃት። እስከተመረቅንበት ጊዜ ድረስ አውርቻት አላውቅም። የምርቃታችን ጊዜ ከአዳራሽ ስወጣ ጠብቃ አንድ ነገር አለችኝ.....‹ከእንግዲህ እኮ አንገናኝም፣ ነገ ለእኔና ለአንተ ሌላ ቀን ነው..ከአንተ ጋ አንድ ማስታወሻ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ አለችኝ።

ዝም ብዬ ፊቷ ቆምኩኝ...ያ ቀን ከረጅም ጊዜ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ፊቷ የቆምኩበት ቀን ነው። በደንብ አየኋት...እንደዚያ ቀን ውብ ሆና አይቻት አላውቅም። ፊቷ ላይ ውበቷን ያደመቁ ብዙ ዓይነት ቀለሞች ይታዩኛል። ቅንድቧ በቀጭን ተቀንድቧል፣ ዓይኖቿ ዙሪያ ገባውን ተኩለዋል። ጉንጮቿ በወዘማ ቀለም ልመዋል። ከንፈሯ እንደምትወደው በማውቀው፣ ሰማይ ቤት ድረስ ይዛው በምትሄደው ቀይ ቀለም ደምቋል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ዓይኖቿ ይስቃሉ፣ ጠንበለል አካሏ ይቁነጠነጣል።

‹ነገ ሲሆን ሁሉም ሌላ ነው...የአሁን ማለዳዎች በኋላ የሚመሹ ናቸው። ነገ በሚደበዝዙ አጋጣሚዎች ልትለያት አንድ ቀን የቀረህን ጓደኛህን አታሳዝናት› ስትል ሰማኋት።

ልቤ አራራልህ አለኝ። በሕይወቴ ሁሉም ቦታ ያለች ሴት ሆና ግን ጨከንኩባት። የነፍሴ ቦታ ቢታይ..የልቤ ስፍራ ቢፈተሽ እሷ ብቻ ናት ግን ፊት ነሳኋት።

ዓይኖቿ ይማጸኑኛል...ዓይኖቼ ይሸሻታል።

ከየት እንዳመጣሁት የማላውቀው እንቢ ልላት የሚያስችል ብዙ ኃይል ነበረኝ። ዕድሜ ለትቸር ሞገስ እንደ አራስ ነብር እንድፈራት አድርጎኛል። በዚያ በመጨረሻ ሰዓት አንድ ፎቶ እንነሳ ብላ ከነጋውኗ ፊቴ ስትቆም ትቻት ነበር የሄድኩት። ያ ቀን ሁሌም ይቆጨኛል። ምነው እሺ ባልኳት ስል አስባለሁ። ዛሬ ላይ ከእሷ ይልቅ እኔ ነበርኩ ያ ፎቶ የሚያስፈልገኝ እላለሁ። ከእሷ ጋር ለመታረቅ ያ ቀን ትክክለኛ ጊዜ ነበር። ያን ያክል ለምን እንደጠላኋት አላውቅም። በጣም የሚገርመው ደግሞ በሸሽኋት በነዚያ ሁሉ ቀን ውስጥ ልታናግረኝ ስትከተለኝ እንደነበረ አስታውሳለሁ።

አሁን ላይ ልቤ ይቅር ብሏት ቢሆን ኖሮ እላለሁ። አሁን ላይ አንድ አይደለም ከእሷ ጋር ለቁጥር የሚታክቱ ፎቶዎች ኖረውኝ ቢሆን እላለሁ። በተለያየንባቸው አስር አመታት ውስጥ ሳላስባት የቀረሁበት ጊዜ አልነበረም። እሷም ይሄን ስለምታውቅ ነው መሰለኝ ትናንትና ዛሬ አንድ ዓይነት አይደሉም ያለችኝ። ከሰው ልጅ ቀድሞ ሕይወት የገባት ሴት ትመስለኛለች። ትናንት ላይ ሆና ዛሬዬን አይታልኛለች። ባሳለፍኩት አስር አመታት ውስጥ ነፍሴ እንደ እሷ የተራበችው ሰው የለም። እኔም በእሷ የተራቆትኩትን ያክል በምንም አልተራቆትኩም። አሁን የት እንዳለች አላውቅም ይሄ ሁሉ ዘመን አልፎ እንኳን ከውስጤ አልደበዘዘችም...ፊቴ ቆማ አንድ ፎቶ እንነሳ እንዳለችኝ እኔም አንድ ቀን ፊቷ ቆሜ እባክሽ ፎቶ እንነሳ የምልበት ቀን ይመጣል እላለሁ።

ምድር ላይ ዳግም እኔና እሷ እዚያ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ፣ እዚያ ክፍል፣ እዚያ አዳራሽ በር ላይ ብንፈጠር እላለሁ። እዚያ ክፍል በትቸር ሞገስ ብንማር እላለሁ። ስለ እሷ የማይሆን ነገር አስባለሁ..

# ዓለም አቀፍ

## ፕሬዚዳንት ባይደን 1.2 ቢሊዮን ዶላር የተማሪዎችን ዕዳ ሰረዙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የባይደን አስተዳደር 153 ሺህ ተበዳሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ 1.2 ቢሊዮን ዶላር የትምህርት ዕዳ መሰረዙን አስታወቀ።

የአሜሪካ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከዚህ ቀደም ከ40 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ አሜሪካውያን የትምህርት ዕዳቸውን ለመሰረዝ ፕሬዚዳንት ባይደን አቅርበው የነበሩትን ዕቅድ ማገዱ ይታወሳል።

ፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት ባይደን ሥልጣናቸውን ተላልፈው በቢሊዮን የሚቆጠር የትምህርት ዕዳ ለመሰረዝ መወሰናቸው ትክክል አይደለም ሲል ቀልብሶታል።

የአሁኑ ዕዳ ስረዛ የሚመለከተው በክፍያ ዕቅድ ውስጥ የተካተቱ እና የተወሰኑ መስፈርቶችን ለሚያሟሉ ብቻ ተግባራዊ ይሆናል።

የዕዳ ስረዛው የሚመለከታቸው በባይደን አስተዳደር በተዘረጋው የፍቃደኝነት የክፍያ ዕቅድ ውስጥ የተመዘገቡና ቢያንስ ለ10 ዓመታት ክፍያ ሲፈጽሙ የቆዩ እና መጀመሪያውኑ 12 ሺህ ዶላር ወይም ከዚያ በታች የተበደሩትን የሚመለከት ይሆናል።

የዕዳ ስረዛው የሚመለከታቸው አሜሪካውያን ከተነገራቸው በኋላም ወዲያውኑ ተፈጻሚ እንደሚሆንም ተገልጿል።

«በተለይም አነስተኛ ዕዳ ያለባቸውን የማኅበረሰብ ኮሌጆች የቀድሞ ተማሪዎች እና ሌሎች ተበዳሪዎችን የሚጠቅም ይሆናል። አብዛኛውንም ከትምህርት ዕዳ በፍጥነት ነፃ አውጥቶ ወደ ትክክለኛው መስመር ያስገባቸዋል» ሲልም ዋይት ሃውስ በመግለጫው አትቷል።

በትምህርት ዲፓርትመንት መረጃ መሠረት በባይደን




አስተዳደር በተቋቋመው የክፍያ ዕቅድ ውስጥ የተመዘገቡ አሜሪካውያን ቁጥር ሰባት ነጥብ አምስት ሚሊዮን መሆኑን ነው።

በዚህ ዕቅድ ውስጥ የተመዘገቡት ሁሉም ሰዎች ከ20-25 ዓመታት ውስጥ ክፍያ ከከፈሉ በኋላ በዕዳ ስረዛ ውስጥ ለመካተት ብቁ ይሆናሉ።

ሆኖም ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን አነስተኛ ዕዳ ላለባቸው ግለሰቦች ጊዜውን በማሳጠር ለአስር ዓመታት ያህል ብድራቸውን የከፈሉ ሰዎች በዕዳ ስረዛው ፕሮግራም መካተት እንዲችሉ አድርገዋል።

የሀገሪቱ የትምህርት ዲፓርትመንት በዕዳ ስረዛው ለመካተት ብቁ የሆኑትን ነገር ግን በዚህ የክፍያ ዕቅድ ውስጥ ያልተመዘገቡ ሰዎችን ማነጋገር እንደሚጀምርም ተገልጿል።

ባይደን እስካሁን ድረስ ፕሬዚዳንታዊ ሥልጣንን በመጠቀም 3.9 ሚሊዮን ለሚጠጉ ሰዎች 138 ቢሊዮን ዶላር የትምህርት ዕዳቸውን መሰረዛቸውንም ዋይት ሃውስ ገልጿል።

የአሜሪካ የትምህርት ሥርዓትን በሚያጠናው የትምህርት መረጃ ኢኒሺዬቲቭ መሠረት የአሜሪካ የትምህርት ዕዳ አንድ ነጥብ 77 ትሪሊዮን እንዲሁም አንድ ሰው በአማካኝ ከ37 ሺህ ዶላር በላይ ብድር አለበት።

ጆ ባይደን በምርጫ ቅስቀሳ ሰሞን ዕዳ መሰረዛቸው ለምርጫው እንዲያመቻቸው ነው የሚሉ አልጠፉም።

እሳቸው ግን በቅርቡ የ26 ሰከንድ ርዝማኔ ባለው የቪዲዮ መልዕክት አርፍደው የቲክቶክ ተጠቃሚ መሆናቸውን ይፋ አድርገው ቅስቀሳቸውን አጣጡፈውታል።

የፕሬዚዳንቱ የቲክቶክ ተጠቃሚነት ወሬ የተሰማው አጫጭር የቪዲዮ ምስሎች መጋሪያው የማኅበራዊ ትስስር መድረክ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአብዛኛው በሪፐብሊካን ፓርቲው ወገኖች እና በባይደን አስተዳደር ጭምር በዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ከፍተኛ ትችት ሲሰነዘርበት ከቆየ በኋላ ነው።

በቻይናው ኩባንያ ባይት-ዳንስ ንብረት የሆነው ቲክቶክ በበርካታ የዩናይትድ ስቴትስ ፖለቲከኞች ‘የቤጂንግ የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ ነው’ የሚል ክስ ሲቀርብበት የቆየ ነው። ይሁን እንጂ ኩባንያው ውንጀላውን አጥብቆ ያስተባብላል።

በባይደን የምርጫ ዘመቻ ስም የወጣው የእሁዱ ቪዲዮ ከዴሞክራት ፓርቲው ወገን የሆኑት የ81 አመቱ ፕሬዚዳንት ባይደን፡ ከፖለቲካ ነክ ጉዳዮች እስከ የዩናይትድ ስቴትስ እግር ኳስ የፍጻሜ ዋንጫ ውድድር በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ያላቸውን ሃሳብ በጨዋታ ለዛ ሲያነሱ ያሳያል።

ሱፐር ቦል በመባል ከሚታወቀው የውድድሩ የፍጻሜ ጨዋታ እና የተለየ ትኩረት ዘንድሮ ለዚያ በተሰየመው ድምጻዊ አሸር በተመራው ከሚስበው የጨዋታው አጋማሽ ትርኢት የቱን እንደሚመርጡ ተጠይቀው፣ ‘ጨዋታውን መመልከት’ ብለዋል።

ኮከብ የፖፕ ሙዚቃ አቀንቃኟ ቴይለር ስዊፍት ዝነኛነቷን ተጠቅማ ባይደንን ለመጥቀም የጠነሰሰችው ‘ምስጢራዊ ውጥን አለ’ የሚለውን የቀኝ አጥባቂዎች የሴራ ወሬ አስመልክቶም ለተጠየቁት “ብነግርህ ችግር ውስጥ እገባለሁ”ሲሉ በጨዋታ መልሰዋል።

በተያያዘ በ2024ቱ የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ጵንስ የማቋረጥ መብት ለመራጮች ቁልፍ ጉዳይ እንደሚሆን ዋይት ሃውስ ማስታወቁ የሚታወስ ነው።

# የዲፕሎማሲ ስኬታችንን የበለጠ ለማጎልበት

**በመላኩ ሙሉዓለም ቀ.**
**በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የስልጠና ዳይሬክተር ጄኔራል**
melakumulu@yahoo.com

በዓለማችን የሚገኙ ሀገራት ፈርጀ ብዙ የዲፕሎማሲ ግንኙነት በማድረግ የጋራ ጉዳዮቻቸውን ይከውናሉ፤ አለመግባባት ሲፈጠርም በውይይትና በድርድር ይፈቱታል፡፡ ሁልጊዜ የዲፕሎማሲ ሥራ ስኬታማ ላይሆን ስለሚችል ወደ ጦርነትም የሚገቡበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ከጦርነት በኋላ የሰላም መፍጠሪያው ደግሞ ያው ዲፕሎማሲ ነው። ዲፕሎማሲ የሁለትዮሽ እና የባለብዙ ወገን ቅርጽ ሊኖረው የሚችል ሲሆን መንግሥታት እንደየፈርጁ ይጠቀሙታል፡፡

የዲፕሎማሲ ሥራ መደበኛ ከሆነው በተጨማሪ በበርካታ አካላት ሊከናወን ይችላል፡፡ ለአብነት ያክል በሃይማኖት ተቋማት፤በአሰላሳይ ተቋማት (Think tank)፤ በሲቪክ ማህበራት፤በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የንግዱ ሴክተር ውጭ ሀገር ከሚገኙ አቻ ተቋማት ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በመፍጠር የጋራ ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡

አንዳንድ ተመራማሪዎች የዲፕሎማሲ ተግባር የሚያከናውኑትን እስከ ዘጠኝ መደድ (track) ያደርሱታል፡፡ ለዚህ ጽሁፍ የዲፕሎማሲ ሥራ የሚያከናውኑትን አካላት በሁለት ብቻ እየከፈሉ የሚተነትኑትን ምሁራን ጥናት የምጠቀም ሲሆን እነዚህም በመንግሥት የሚከናወነውን መደድ አንድ በማለት፤ መንግሥታዊ አካላት ባልሆኑት የሚከናወነውን ዲፕሎማሲ መደድ ሁለት በማለት ይሆናል፡፡

መንግሥታት የዲፕሎማሲን ሥራ የሚመሩበት ዋናው ተቋም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ነው። በመሆኑም መንግሥት ከሌላ መንግሥት ጋር የሚያከናውነው ዲፕሎማሲ መደድ አንድ ዲፕሎማሲ ሲሆን መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በሌሎች ሀገራት ከሚገኙ መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር የሚያከናውኑት ዲፕሎማሲ መደድ ሁለት ዲፕሎማሲ (Track 2 Diplomacy) ይባላል፡፡

እነዚህ ሁለት የዲፕሎማሲ መደዶች(Track1 and Track2 ) በየራሳቸው መቆምና ተነጣጥለው መስራት የሚችሉ ሲሆን፤ በሁለቱ መካከል የቅንጅት ሥራ የሚያከናውኑ ከሆነ ደግሞ መደደ አንድ ነጥብ አምስት ዲፕሎማሲ (Track 1.5 Diplomacy) ይባላል:: የዚህም ጽሁፍ ትኩረት መደድ አንድ ነጥብ አምስት ዲፕሎማሲ ሲሆን፤ ከዚህ በኋላ 1.5 ዲፕሎማሲ በሚል ይጠቀሳል።

የ1.5 ዲፕሎማሲ ፅንሰ ሃሳብ በመንግሥት ብቻ የሚከናወን ዲፕሎማሲ ብዙ ክፍተቶች ሊኖሩት ይችላሉ፤ በመሆኑም መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት የዲፕሎማሲ ሥራ ቢታገዝ የበለጠ ውጤታማ ሊሆን ይችላል የሚል መነሻና እሳቤ የያዘ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን በሁሉም የዲፕሎማሲ ሥራ ውስጥ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት መግባት አለባቸው ማለት ሳይሆን በተመረጡ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የመንግሥትን የዲፕሎማሲ ሥራ እንዲያግዙ ሊደረግ እንደሚገባ አጽንኦት ይሰጣል፡፡

ለአብነት ያክል የአየር ንብረት ለውጥ፣ በሰላም ግንባታ፣ በዘላቂ ልማት እና በዓለም አቀፍ ጤና ጉዳዮች ላይ ያሉ ብዙ ዓለም አቀፍ ፈተናዎች በርካታ ባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ የትብብር እና አካታች አካሄድ ስለሚፈልጉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የአካባቢ ማህበረሰቦች፣ የአካባቢው ተወላጆች እና ሌሎች የሲቪል ማህበረሰብ ተዋናዮች ብዙ ጊዜ ጠቃሚ እውቀት እና አመለካከቶች ስላላቸው ለተወሳሰቡ ዓለም አቀፍ ችግሮች መፍትሄ ለመፈለግ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ።

በዚህ የዲፕሎማሲ አሰራር የመንግሥት ባለስልጣናት፣ ባለሙያዎች እና የሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮች በተለያዩ መንገዶች ማለትም በምክክር፣ኮንፈረንስ እና ወርክሾፖች ተገናኝተው በጋራ ጉዳዮች ላይ የሚወያዩበት እና ውስብስብ ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችን ለመፍታት የሚያገለግል ነው። ይህ አካሄድ ከመደበኛው የመንግሥት የዲፕሎማሲ ተዋናዮች ባሻገር የተለያዩ ድምፆችን እና አመለካከቶችን በማካተት የዲፕሎማሲያዊ ሂደቶችን ውጤታማነት እና አካታችነት ለማሳደግ የሚያስችል ነው።

> **መንግሥታት የዲፕሎማሲን ሥራ የሚመሩበት ዋናው ተቋም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ነው። በመሆኑም መንግሥት ከሌላ መንግሥት ጋር የሚያከናውነው ዲፕሎማሲ መደድ አንድ ዲፕሎማሲ ሲሆን መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በሌሎች ሀገራት ከሚገኙ መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር የሚያከናውኑት ዲፕሎማሲ መደድ ሁለት ዲፕሎማሲ (Track 2 Diplomacy) ይባላል**

ከዚህም በተጨማሪ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ግንዛቤያቸውን፣ ምርምሮችን እና ምርጥ ተሞክሮዎቻቸውን ለመደበኛዎቹ ዲፕሎማቶች የሚያካፍሉበት መድረክ ይፈጥራል። ይህ የእውቀት ልውውጥ ዲፕሎማሲያዊ ውይይቶችን የሚያበለጽግ እና የበለጠ በመረጃ የተደገፈ ውሳኔ ለማድረግ ያስችላል።

በጋራ ተግዳሮቶች ላይ ቀጣይነት ያለው ተሳትፎን በማድረግ የትብብር እና የጋራ እርምጃ ለመውሰድ ያስችላል። የኮቪድ ወረርሽኝ በተከሰተበት ወቅት መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በቅንጅት ይሰሩ እንደነበር አንዱ ማሳያ ነው፡፡ በአካባቢ ጥበቃ፤ በሳይንስ፤ ስደት እና ወዘተ የሥራ መስኮች ውስጥ መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ውስጥ ከፍተኛ እውቀትና ተሞክሮ ስለሚኖር ለዲፕሎማሲ ግብአት እውቀታቸውን መጠቀሙ መልካም ነው፡፡

በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ቅንጅት የሚከናወን ዲፕሎማሲ የአካባቢ ማህበረሰቦች ድምጽ እና ስጋቶች ተገቢ ትኩረት እንዲያገኙ ከታች ወደ ላይ (Bottom-Up Approach) ያለውን አካሄድ ትኩረት ይሰጣል። መንግሥት ከመንግሥት ጋር የሚያደርገው ዲፕሎማሲ በአብዛኛው ከላይ ወደታች የሚፈስ ነው (Top-Down Approach)::

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ውሳኔዎች በአካባቢው ማህበረሰቦች ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ እንደሚኖራቸው እና የእነሱ ተሳትፎ ውጤታማ እና ዘላቂ መፍትሄዎችን ለማግኘት ወሳኝ ሊሆን ይችላል። መንግሥታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር 1.5 ዲፕሎማሲ የእነዚህን ማህበረሰቦች ፍላጎቶች ግምት ውስጥ ለማስገባት ያስችላል፡፡ ይህ አሰራር በመደበኛው የዲፕሎማሲ መስመሮች ውስጥ ላይገኙ የሚችሉ የፈጠራ አስተሳሰብን፣ ሙከራዎችን እና አማራጭ አመለካከቶችን ለማየት ያግዛል።

መደድ 1.5 ዲፕሎማሲ በሀገሮች መሀከል የሚከሰትን ግጭት ለማስቆም ይረዳል፡፡ በተለይ መንግሥታዊ የዲፕሎማሲ መስመሮች በፖለቲካ ውጥረቶችና ግጭቶች እንዳይደናቀፍ ሊያግዝ ይችላል። ይህ ዲፕሎማሲ የግጭት አፈታት ጥረቶች አማራጭ የውይይት እና የድርድር መንገዶችን በማቅረብ ሚና ይጫወታል።

ይፋዊ ዲፕሎማሲያዊ ድርድር በፖለቲካ ማነቆዎች ወይም መተማመን ማጣት ሊደናቀፍ በሚችልበት ሁኔታ፣መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትን በ1.5 ዲፕሎማሲ ማሳተፍ መደበኛ ላልሆኑ ውይይቶች፣የመተማመን ግንባታ እርምጃዎች እና የሽምግልና ጥረቶች እድልን የመፍጠር እና የመግባባት መድረኮችን ማመቻቸት ይችላል። ይህ የሰላም ግንባታ ሂደቶችን ለማከናወን እና ግጭቶችን ለመፍታት አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ቅንጅት የሚከናወን ዲፕሎማሲ የዲፕሎማሲያዊ ስኬቶችንና ክፍተቶችን ለመከታተልና ለመገምገም አስፈላጊ ከመሆኑም ባሻገር ዓለም አቀፋዊ ተግዳሮቶችን በመቅረፍ ላይ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የዲፕሎማሲያዊ ጥረቶችን ውጤታማነት ለመገምገም እና መሻሻል ያለባቸውን ቦታዎች ለመለየት አመለካከቶችን፣ መለኪያዎችን እና የግምገማ ማዕቀፎችን መጠቀምን ይጠይቃል። ክትትል እና ግምገማ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ መስጠት፣ ካለፉት ተሞክሮዎች መማር እና ዲፕሎማሲያዊ ስልቶችን በማጣጣም የተሻለ ውጤት ለማምጣት ያስችላል።

የመደድ 1.5 ዲፕሎማሲ አሰራር በሁለትዮሽና በባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ ውስጥ ሊከወን የሚችል እንደሆነ ከላይ ተጠቅሷል፡፡ የባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ ማሳያ ከሆነው ውስጥ አንዱ የአየር ንብረት ጋር በተያያዘ የሚከሰትን አደጋ ለመከላከል የፓሪሱ ስምምነት መፈረሙ ይታወሳል፡፡ ይህ ዲፕሎማሲ ከስር ወደ ላይ (Bottom-Up Approach) ያለውን አካሄድ የተከተለ ነው፡፡

በመሆኑም የ1.5 ዲፕሎማሲ ስኬት አንዱ ማሳያ እ.ኤ.አ ታኅሣሥ 12 ቀን በ2015 ከአንድ መቶ ዘጠና ሀገሮች በላይ በሚሆኑ መንግሥታት የፀደቀው የፓሪሱ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ነው። የፓሪሱ ስምምነት የመንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትን በማሳተፍ ዲፕሎማሲያዊ ሂደቱ ዓለም አቀፋዊ የአየር ንብረት ፈተና ለመቅረፍ ጥረት የተደረገበት ነው።

በዚህ ስምምነት ሀገሮች የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትሉ በካይ ጋዞችን እንዲቀንሱና የዓለም ሙቀት መጨመርን እንዲቆጣጠሩ የተስማሙበት ነው፡፡ ይህም የተባበሩት መንግሥታት ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት እቅድ (Sustainable Development Goals) ስኬት ለማምጣት አንዱ የአየር ንብረት ቀውስን መከላከል በመሆኑ ነው፡፡

ከአየር ንብረት ለውጥ በተጨማሪ 1.5 ዲፕሎማሲ በተለይ ከሀገር አቀፍ ድንበሮች ባሻገር ያሉትን ተግዳሮቶች ለመፍታት ጠቃሚ ነው። እንደ ፍልሰትና ስደት፣ ሽብርተኝነት፣ የሳይበር አደጋዎች እና ወረርሽኞች ያሉ ጉዳዮች በበርካታ ባለድርሻ አካላት መካከል የትብብር ጥረቶችን ይፈልጋሉ። 1.5 ዲፕሎማሲ የመንግሥት ያልሆኑ ተዋናዮች በእውቀታቸው እና በኔትወርኩ አማካኝነት እነዚህን ውስብስብ ፈተናዎች በብቃት ለመወጣት ጠቃሚ ግንዛቤዎችን እና ግብአቶችን ማበርከት ይችላል።

በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ቅንጅት የሚከናወን ዲፕሎማሲ ተጠያቂነትን እና ግልጸኝነትን በዓለም አቀፍ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ እንዲኖር ያግዛል። ሰፋ ያሉ ተዋናዮችን በማሳተፍ የዲፕሎማሲያዊ ሂደቶችን መመርመር እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተዋናዮች ብዙውን ጊዜ የተለያዩ አመለካከቶችን በማምጣት ለግልጽነት፣ ለተጠያቂነት እና ለሰብአዊ መብቶች እና የአካባቢ ጥበቃ ደረጃዎች መጠበቅ ያግዛሉ።

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መደበኛውን ዲፕሎማሲ በእውቀት፣ በገንዘብ፣ በማቴሪያል፣ በቴክኖሎጂ፣ አጋርነትን በማስፋት፣ የሕዝብን ድጋፍ በማሰባሰብ፣ ተጽእኖ በመፍጠር እና ወዘተ ድጋፎችን በመስጠት የተሳካ ዲፕሎማሲ ለማከናወን ያግዛሉ፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሁሉም የዲፕሎማሲ ተግባራት ላይ እንዲገቡ ሳይሆን በተጠኑና በተመረጡ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ።የዲፕሎማሲ ሥራም ምስጢራዊነት ከሚጠይቁ የሥራ መስኮች ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው እንደመሆኑ መጠን 1.5 ዲፕሎማሲ ሲከናወን የዲፕሎማሲ ድጋፍ በማግኘትና በምስጢራዊነት መካከል ያለውን ሚዛን በጥንቃቄ መጠበቅና መምራት ያስፈልጋል፡፡

መደድ 1.5 ዲፕሎማሲ ለኢትዮጵያ ያለው ጥቅም በርካታ ነው፡፡ በተለይ የሀገራችን ወጣቶች በየአረብ ሀገር ለሚደርስባቸው ችግር መፍትሄ በመስጠት በኩል መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአየር ንብረት ጥበቃ፤ በሰላምና ጸጥታ ተግባር፤ በድንበር ተሻጋሪ ሀብቶች፣ በሳይንስ ዲፕሎማሲ፤ በዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ፤ በኢኮኖሚና ፐብሊክ ዲፕሎማሲና ወዘተ ዙሪያ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲሳተፉ ማድረጉ በመንግሥት ላይ ያለውን ጫና ለመቀነስ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም መደድ 1.5 ዲፕሎማሲ ሥራ የሚያስፈልጉባቸው የዲፕሎማሲ መስኮች በጥናትና ምርምር በመለየትና ስትራቴጂ በማዘጋጀት መተግበር በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ይህ የዲፕሎማሲ አሰራር አንዱ በሥራ ጫና ሲደክም ሌላው ተመልካች የማይሆንበት በመሆኑ የትብብር መንፈስ መፍጠር፤ የባለቤትነትን እና ያገባኛል ስሜትንም መፍጠር የሚችል በመሆኑ ፈርጀ ብዙ ዲፕሎማሲ (holistic diplomacy) ለማከናወን ያግዛል፡፡

ለማጠቃለል ያህል 1.5 ዲፕሎማሲ ኦፊሴላዊ ዲፕሎማሲ ክፍተት ለመሙላት እና ለችግሮች መፍትሄ ለማምጣት ያግዛል እንጂ የመንግሥት ለመንግሥት ይፋዊ የዲፕሎማሲ ግንኙነትን አይተካም፡፡ ሆኖም ግን በርካታ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን፤ ከእነዚህም ውስጥ ሀገር አቀፍ፣ አህጉር አቀፍ እና ዓለም አቀፋዊ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት መካከል ትብብርን፣ ውይይትን እና የጋራ መግባባትን ለማስፋፋት፣ ውስብስብ ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችን ለመፍታት፣ ሕዝባዊ ድጋፍን በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ለማሰባሰብ ፣ ዲፕሎማሲያዊ ተጽዕኖ ለማሳደር ይጠቅማል።

የውጭ ንግድና ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ ሬሚታንስን ለመጨመር፣ የአደጉ ሀገራትን የዲፕሎማሲ ጫና ለመቋቋም፣ የዲፕሎማሲ ግንዛቤን ለማሳደግ፣ በዲፕሎማሲ ዘርፍ የሕዝብ ግፊትን ለመፍጠር፣ የእውቀት አቅርቦትን ለመፍጠር፣ አካታችነትን ለማሳደግ፣ የፈጠራ ዘዴዎችን ለዲፕሎማሲ ለመጠቀም፣ በዲፕሎማሲ ዘርፍ አቅም ግንባታ ለማስፋት ይረዳል።

መንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት መካከል ድልድይ በመገንባት የሥራ ቅንጅትንና ትብብርን ለመፍጠር፣የመረጃ ልውውጥን ለማስፋት፣ የሀብት ማሰባሰብ ለማገዝ፣አዳዲስ መፍትሄዎችን ለመቃኘትና ለመጠቀም፣ የሀገር በቀል የዕውቀት ሥርዓቶችን ለዲፕሎማሲ ሥራ እንደግብአት ለመጠቀም እና ወዘተ ያግዛል፡፡ ይህንን ታሳቢ በማድረግ 1.5 ዲፕሎማሲ አሰራርን በጥናትና ምርምር ላይ ተመስርቶ መተግበር የሀገራችንን የዲፕሎማሲ ተግባር አንድ እርምጃ ወደፊት ይወስደዋል የሚል እምነት አለኝ ፡፡

Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን

# ዓርብ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## አንደኛው ዙር ብሔራዊ የቦክስ ቻምፒዮና ነገ ይጠናቀቃል

**ብርሃን ፈይሳ**

በኢትዮጵያ ቦክስ ፌዴሬሽን አዘጋጅነት እየተካሄደ የሚገኘው አንደኛው ዙር ብሔራዊ የቦክስ ቻምፒዮና ነገ ይጠናቀቃል፡፡ ጠንካራ ፉክክር ሲያስተናግድ የቆየው ይህ የቡጢ ቻምፒዮና በተለያዩ ዓለም አቀፍ ውድድሮች ኢትዮጵያን የሚወክሉ ቦክሰኞች እንደሚመረጡበት ከፌዴሬሽኑ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡

በአራት ዙሮች የሚካሄደው ብሔራዊ የቦክስ ቻምፒዮና የዘንድሮውን ዓመት የመጀመሪያ ዙር ውድድር በራስ ኃይሉ ትምህርትና ስልጠና ማዕከል በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ከየካቲት 12/2016 ዓ.ም አንስቶ በደማቅ ሁኔታ ሲከናወን የቆየው ውድድር ነገ እንደሚፈፀምም ታውቋል።

በውድድሩ ከተሳተፉ ዘጠኝ የቦክስ ክለቦች መካከል ስድስት የሚሆኑት በሁለቱም ጾታ ተፎካካሪዎች ያቀረቡ ሲሆን፤ የግል ተወዳዳሪዎችን ጨምሮ በድምሩ 106 ቦክሰኞች የቻምፒዮናው ተሳታፊ መሆናቸው ተጠቁሟል።አዲስ አበባ ፖሊስ፣ አሜድላ፣ ፌዴራል ማረሚያ ቤቶች፣ ኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፣ ፋሲል ከተማ፣ ድሬዳዋ ከተማ፣ ወላይታ ጦና፣ ሀዲያ ሆሳዕና እና የጋሞ ክለቦች የውድድሩ ተሳታፊ ናቸው፡፡

በጠንካራ ፍልሚያዎች አጓጊ ፉክክር ታጅቦ እየተካሄደ በሚገኘው በዚህ ውድድር ላይ የተሻለ ብቃት ያሳዩ ተወዳዳሪዎች ለብሔራዊ ቡድን በመመረጥ በቅርቡ ለሚካሄዱ አህጉርና ሀገር አቀፍ ውድድሮች ላይ ይካፈላሉ፡፡ በዚህም መሰረት በፓሪስ ለሚካሄደው የ2024 ኦሊምፒክ የማጣሪያ ውድድር ከሳምንት በኋላ በጣሊያን የሚደረግ ሲሆን፤ ቀጥሎ በሚካሄደው የመላ አፍሪካ ጨዋታዎች ላይም ኢትዮጵያን የሚወክሉ ይሆናል፡፡ ሌላኛው ውድድር ደግሞ በደቡብ አፍሪካ የሚደረግ የማንዴላ ካፕ እንዲሁም ሌሎች ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ተሳታፊ እንደሚሆኑ የኢትዮጵያ ቦክስ ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ስንታየሁ ማሩ ገልጸዋል፡፡



**አንደኛው ዙር ብሔራዊ የቦክስ ቻምፒዮና ጠንካራ ፉክክር እያስተናገደ ይገኛል፤**

ውድድሩ በተለያዩ ክብደቶች እየተካሄደ ሲሆን፤ በወንዶች መካከል በ48 ፣ በ51 ፣ በ54 ፣ በ57፣ በ60፣ በ63.5፣ በ69፣ በ75፣ በ80፣ በ92 እና ከ92 ኪሎ ግራም በላይ በርካታ ፉክክሮች ተደርገዋል፡ ፡ በሴቶች ደግሞ በ48፣ በ50 ፣ በ60 ፣ በ63 እና በ67 ኪሎ ግራም ቦክሰኞች ሲፎካከሩ ቆይተዋል፡፡

በውድድሩ በተለይም ወጣትና ተተኪ ቦክሰኞች ያላቸውን ተስፋ አሳይተዋል፡፡ ከዚህ ቀደም ይነሳ የነበረውን የልምድ ማነስ ችግር ለመቅረፍም መሰል ውድድሮች መካሄዳቸው ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው የተጠቆመ ሲሆን፤ በአህጉር እና ዓለም አቀፍ ውድድሮች በሚኖራቸው ተሳትፎም ከዚህ ቀደም በስፖርቱ የታየውን ውጤታማነት ማሳደግ ይቻላል ተብሎ ታምኖበታል፡፡

ይህ ውድድር ኢትዮጵያ የአፍሪካን ቦክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንትነት መምራት ከጀመረች በኋላ የተካሄደ የመጀመሪያው ውድድር ሲሆን፤ በስፖርቱ ጥሩ መነቃቃት መፈጠሩን ለመታዘብ ተችሏል፡፡ የክለቦች ቁጥር መጨመርና በፉክክሩ ላይ ተሳታፊ የሆኑ ቦክሰኞች ተሳትፎ ለስፖርቱ እድገት ተስፋ የታየበት ሆኗል፡፡

ቻምፒዮናውን ከዚህ ቀደም ከተካሄዱት ልዩ የሚያደርገው የውድድሩ ተሳታፊ ቦክሰኞች ሙሉ የጤና ምርመራ ማድረግ በመቻሉ እንደሆነ የጽህፈት ቤት ኃላፊው ገልፀዋል፡፡ ቦክስ ከፍልሚያ ስፖርቶች መካከል አንዱ እንደመሆኑ በተለይ በንክኪ፣ በላብ፣ በደም... የሚተላለፉ የጉበት እና ኤች አይቪ ኤድስ በሽታዎችን እንዲሁም እርግዝናን በአስገዳጅ ሁኔታ የሚለይበት ምርመራ ለሁሉም ተወዳዳሪዎች ተደርጓል፡፡ ይህ ሁኔታ በሀገር ውስጥ በሚደረጉ ውድድሮች ጠንካራ ባይሆንም በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ ውድድሮች ግን ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ከዚህ ቻምፒዮና አንስቶ ትኩረት እንደሚሰጠው የተገለጸ ሲሆን፤ በምርመራው በሽታዎቹ እንዳለባቸው የተረጋገጠባቸው ቦክሰኞችም ፌዴሬሽኑ ባቋቋመው የህክምና ቡድን አማካኝነት የጤና እንዲሁም የስነልቦና ክትትል ይደረግላቸዋል፡፡

ከክለቦቻቸውና አሰልጣኞች ጋርም ከውጤት ባለፈ ጤናቸውን ቅድሚያ ሰጥተው አገግመው በሚመለሱበት ሁኔታ ላይ ንግግር መደረጉንም አቶ ስንታየሁ ተናግረዋል።

በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች በመዘዋወር በአራት ዙር የሚደረገው ብሔራዊ የቦክስ ቻምፒዮና ዘንድሮ መነሻውን አዲስ አበባ በማድረግ ከየካቲት 12/2016 ዓ.ም አንስቶ ሲካሄድ ቆይቶ ነገ ፍጻሜውን ያገኛል፡፡ ቀጣዮቹ ቻምፒዮናዎች ደግሞ በድሬዳዋ እና አርባ ምንጭ ከተሞች በማድረግ ማጠቃለያውን አዲስ አበባ ላይ ለማካሄድ መታሰቡንም ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡